ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችእና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

# በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂልእና ፍላጎትን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ውባለም አዲሱ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ የሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ 2016

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርትክፍል

ድህረ ምረቃፕሮግራም

# በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል እና ፍላጎትን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትበ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት

በ

ውባለም አዲሱ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነ ዘዴ የሁለተኛ ድግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ግዴታዎች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት

አማካሪ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ ጥበቡ ሽቴ(ዶ/ር)

ነሐሴ 2016

ጅማ ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

# የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

# ድህረ ምረቃፕሮግራም

በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል እና ፍላጎትን ለማዳበር ያለው ሚና፣በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስና ሂማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት በውባለም አዲሱ የቀረበን ጥናታዊ ሥራ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት በማሟላቱ በፊርማችን ተረጋግጦ ተፈርሟል።

የፈተና ቦርድ አባላት

-አማካሪ ........................................................ፊርማ ..........ቀን ................

-የውጭ ፈታኝ ..................................................ፊርማ...........ቀን ...............

-የውስጥ ፈታኝ ................................................ፊርማ..........ቀን ...............

# የአጥኚዋ ማረጋገጫ

በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል እ ፍላጎትን ለማዳበር ያለው ሚና፣በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ እና ሂማኒቲስ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ በአማርኛ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበው ይህ ጥናታዊ ሥራ ለመሥራት በርካታ ምንጮችን የተጠቀምኩ ሲሆን እነዚህን ምንጮችም በአግባቡ በዋቢ ውስጥ ጠቅሻለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ሥራ የራሴ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ..........................................

ፊርማ .......................................

ቀን .......................................

# ምስጋና

በቅድሚያ በነገሮች ሁሉ ለረዳኝ ለልዑል እግዚያብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠል ጥናቱ ከጅማሬው እስከ ፍጻሜው ለስኬት እንዲበቃ ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፣ስህተቴን በማረም፣ ለስራዬ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ለጊዜያቸውና ለጉልበታቸው ሳይሳሱ ጥናቱ ትክክለኛውን አቅጣጫ እንዲይዝ የማማከር እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡በተጨማሪም ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ ረዳት አማካሪዬ ዶ/ር ጥበቡ ሽቴ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም የዚህን ጥናት ወጪ በመሸፈን ከፍተኛ እገዛ ላደረገልኝ ለጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ መሰጋና አቀርባለሁ፡፡ በሌላ በኩል ለስራዬ መሳካት የሀሳብ እና የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ከጎኔ ላልተለየኝ ባለቤቴ መለሰ ገብሬ ምስጋናዬ ወደር የለውም፡፡ በመጨረሻም ትምህርቱን ላስተማረልኝ መምህር ዘሪሁን በቀለ፣ ፈተናዎችን በማረም፣ አስተያየቶችን በመስጠት ሙያዊ እገዛቸው ላልተለየኝ ለአሰንዳቦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ለጥናቱ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝን የአሰንዳቦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

## ማውጫ

ምስጋና……………………………………………………………………………i
ማውጫ ........................................................................................ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ..........................................................................iv
አጠቃሎ.......................................................................................iv
ምዕራፍ አንድ ................................................................................ 1
መግቢያ……………………………………………………………………...1
1.1 የጥናቱዳራ…………..……………………………………………………...1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ................................................................ 6
1.3 የጥናቱ መላምት .......................................................................... 8
1.4 የጥናቱ ዓላማ ............................................................................. 8
1.4.1 ንዑስ አላማ………………………………………………………………..8
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ....................................................................... 8
1.6 የጥናቱ ወሰን .............................................................................. 9
1.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች ........................................ 9
1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች…………………………………………………………9
1.7.2 የተወሰዱ መፍትሔዎች…………..………………………………………10
ምዕራፍ ሁለት .............................................................................. 11
ክለሳ ድርሳናት ............................................................................. 11
2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች.................................................................. 11
2.1.1 የመጻፍ ክሂል ምንነት ................................................................ 11
2.1.2 መጻፍን ማስተማር አስፈላጊነት ....................................................... 12
2.1.3 ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ያለው ሚና ........................................ 13
2.1.3.1 ክሂልን ለማዳበር ................................................................... 14
2.1.3.2 የአዕምሮ እድገትን ለማምጣት ...................................................... 14
2.1.3.3 እውቀትን ለማዳበር ................................................................ 14
2.1.4 ስነ-ጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት............................... 15
2.1.4.1 ስነ-ጽሁፍ በእውነተኛ ቋንቋ የሚቀርብና ዋጋ ያለው መሆኑ ...................... 15
2.1.4.2 ስነ-ጽሁፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለጸገ መሆኑ ............................ 15
2.1.4.3 ስነ-ጽሁፍ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳድግ በመሆኑ .......................... 16
2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍ ................................................................. 17
2.3 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ................................................................ 20
ምዕራፍ ሶስት .............................................................................. 24

የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ........ 24
3.1 የጥናቱ ዘዴ ........ 24
3.2 የጥናቱ አካላይ ........ 24
3.3 የጥናቱ ቦታ (ትምህርት ቤት) አመራረጥ ........ 24
3.4 የተማሪዎች እና የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 25
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 26
3.5.1 ፈተና ........ 26
3.5.2 የፅሑፍ መጠይቅ ........ 27
3.6 የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ ........ 28
3.7 የጥናቱ ሂደት ........ 28
3.8 የማስተማሪያ አህዶች ዝግጅትና ትግበራ ........ 29
3.8.1 የማስተማሪያ አህዶች ዝግጅት ........ 29
3.8.1.1 የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ባገናዘበ መልኩ መምረጥ ........ 29
3.8.1.2 የተማሪዎችን የስነጽሁፍ ዳራዊ ዕውቀት ባገናዘበ መንገድ መምረጥ ........ 31
3.8.1.3 ከስነጽሁፍ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦች ........ 32
3.8.1.4 የማስተማሪያ አህዶች ትግበራ ........ 34
ምዕራፍ አራት ........ 35
የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 35
4.1 የውጤት ትንተና ........ 35
4.2 ከፈተናዎቹ የተገኘ የጥናቱ ውጤት ትንተና ........ 35
4.3 የውጤት ማብራሪያ ........ 43
ምዕራፍ አምስት ........ 46
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ ሀሳብ ........ 46
5.1 ማጠቃለያ ........ 46
5.2 መደምደሚያ ........ 48
5.3 መፍትሄ ሀሳብ ........ 48
አባሪ "ሀ"፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና ........ 54
አባሪ "ለ"፡- የድህረ ትምህርት ፈተና ........ 58
አባሪ "ሐ"፡-በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ ........ 63
አባሪ "መ"፡- የማስተማሪያ አህድ ........ 66
አባሪ "ሠ"፡- የቅድመ እና የድህረ ትምህርት የሙከራ ቡድን የፈተና ውጤት ........ 76
አባሪ "ረ"፡- የቅድመ እና የድህረ ትምህርት የቁጥጥር ቡድን የፈተና ውጤት ........ 77
አባሪ "ሰ"፡- የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት ........ 78

## የሠንጠረዥማውጫ

ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራ ቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት) ……………………………………………….…….....36

ሠንጠረዥ 4.2 የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት)……………………………………………………………37

ሠንጠረዥ 4.3 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት) ……………………………………………………………………38

ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት) …………………………………………………………………..39

ሠንጠረዥ 4.5 የየቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተናጠላዊ ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት") ………………………………………..…………………40

ሠንጠረዥ 4.6 የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና …………………………………………......42

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለውን ሚና በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ በማድረግ መመርመር ነው፡፡ አላማውን ከግብ ለማድረስ ከፊል ሙከራዊ የሚባለውን የምርምር ንድፍ ተጠቅሟል፡፡ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር እና ከአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ሌላ በሆነ ዘዴ በማስተማር ሁለቱን ቡድኖች በቁጥጥርና በሙከራ በመመደብ ለአራት ሳምንታት እንዲማሩ ተደረጓል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ካሉ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በዕድል ሰጪ ንሞና ከተመረጡ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች በ10ኛB እና በ10ኛD ክፍል ያሉ ተማሪዎች ላይ ጥናቱ ተደርጓል፡፡ ከተሳታፊዎች የመጻፍ ክሂል ችሎታን ለመመዘን በቅድመና በድህረ ትምህርት ፈተና መረጃ  ተሰብስቧል፡፡ መረጃዎችም በአማካይ ውጤት፣ በመደበኛ ልይይት፣ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት በገለፃና ድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትኖ የሚከተለው ውጤት ተገኝቷል፡፡ በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት መታየቱ ($p<0.05$) የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያሻሽል ለመረዳት ተችሏል፡፡ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ይህም በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር ምክንያት በተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት (ተነሳሽነት) ላይ ልዩነት እንደሚያሳይ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከጽሁፍ መጠይቁ ውጤትም የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በማስተማሪያነትበመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት እንደሚያሻሽል (እንደሚጨምር) ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና ውጤት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመጻፍ ፍላጎት ለማጎልበት ለተማሪዎች የሚቀርቡ የቋንቋ ትምህርቶች የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መሰረት ያደረጉ (በአጋዥነት የሚጠቀሙ) ቢሆኑ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል አመልክቷል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

ይህ ፅሁፍ ትኩረት የሚያደርገው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር በሚል ርዕስ የተዘጋጀ ጥናት ነው፡፡ የአጥኚዋ የትኩረት አቅጣጫ በኦሞናዳ ወረዳ በአሰንዳቦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የፅህፈት ችሎታ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ይሆናል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች የአማርኛ ቋንቋን ማስተማርየተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ሲሆን የጥናቱ ክፍሎችም በአምስት ምዕራፍ የተከፈለ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ፡- የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መላምት፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎችን የያዘ ሲሆን፣ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ክለሳ ድርሳናት፣ ፅንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች፣ ንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ እና የተዛማጅ ፅሁፍ ቅኝት ያካትታል፣ በምዕራፍ ሦስት ደግሞ የጥናቱ ዘዴ እና አካላይ፣ የጥናቱ ቦታ አመራረጥ፣ የተማሪዎች እና የመምራን ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የመረጃ አደረጃጀት እና አተናተን ዘዴ፣ የጥናቱ ሂደት፣ የማስተማሪያ አሀዶች አዘገጃጀት እና ትግበራ፣ በምዕራፍ አራት ደግሞ የውጤት ትንተና፣ ከፈተናዎቹ የተገኘ የጥናት ውጤት ትንተና፣ የውጤት ማብራሪያ መተንተኛ፣በምዕራፍ አምስት ደግሞ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና የመፍትሔ ሀሳብበውስጡ አካቷል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ጽህፈት ማህበረሰብ በይሁንታ የተስማማባቸው ትዕምርቶች ማለትም ፊደላት ተበጅተውእየተቀናጁ ለዚሁ ተግባር ተብለው በተዘጋጁ ወረቀቶች፣ ወይም ማንኛውም ጠፍጣፋ ገጽታ ባለው ጽሁፉን በሚቀበል ነገር ላይ ሀሳብን አደራጅቶ ወይም አቀናጅቶ የማስፈር ሂደት ነው Kavaliauskiene (2009)፡፡ ጽህፈት ሥዕላዊ ትዕምርቶችን ፈጥሮ በወረቀት፣ ወይም በሌላ ጠፍጣፋ በሆነ ገጽ ላይ ከማስፈር (ከማስቀመጥ) ይበልጥ ተገላጩን ፅንሰ ሀሳብም ያካተተ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሚጻፉት ዐረፍተ ነገሮች እርስ በርሳቸው የሀሳብ ቁርኝት ያላቸው፣ ተጠየቃዊ የሆኑ፣ ፍሰታቸውን የጠበቁ፣ ተለጣጣቂነትና ወጥነት ያላቸው፣ የቋንቋውን ሥርዓት የጠበቁ፣ ጥምረት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ደግሞ ግዴታ ነው፡፡

ጽሕፈት በራሱ ክሂል ነው። ይህም ሲባል ጽሕፈት ከተግባር ጋር ይበልጥ ተያያዥነት ያለው መሆኑ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው በጽህፈት አማካይነት ከሌሎች ጋር ለመግባባት ቢፈልግ አስቀድሞ ይህን ጥበብ መቅሰምና በዚያ ውስጥ ማለፍ ይኖርበታል ማለት ነው። የጽህፈት ክሂል እንደማናቸውም የተቀሩት የቋንቋ ክሂሎች የራሱ የሆነ የተለየ ባህርይ አለው (Sawalemen, 2013)። ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ሁለቱ ማለትም ማንበብና ማዳመጥ የሌሎችን ስሜት የመቀበልና የመረዳት ሁኔታዎችን ስለሚያሳዩ የመረዳት ክሂሎች ሲባሉ መናገርና መፃፍ ደግሞ ተናጋሪው ወይም ፀሐፊው የራሱን ስሜት ለሌሎች የማንፀባረቅ ሁኔታን የሚያመለክትባቸው በመሆናቸው የገለፃ ክሂሎች ሊባሉ ይችላሉ (Keshavarz (2003)።

ጽሁፍ አንድን ልቦናዊ አስተሳሰብ በወረቀት ላይ ለማስፈር እና ወደ ተደራሲያን ለማድረስ የስሜት ሕዋሳትን በቅንጅት በመጠቀም የሚከናወን አካላዊ ተዋፅዖ የሚጨምር አዕምሯዊ ተግባር ነው። ጽሁፍ እንዲተላለፍ የተፈለገን መልዕክት ወይም መረጃ ቅድሚያ በአግባቡ ተገንዝቦ እና ተረድቶ በጽሁፍ በወረቀት ላይ የማስፈር ተግባር እና ሂደት ነው (Kavaliauskiene፣ 2009)።

ፅህፈት የአንድን ቋንቋ አጠቃቀም ሙሉዕ ከሚያደርጉት ዋና ዋና ክሂሎች ውስጥ አንዱ ነው። በመጻፍ ክሒል፣ የአንድ ቋንቋ ተጠቃሚ የሚፈልገውን መልዕክት ያስተላልፋል እንዲሁም መልዕክት ይቀበላል (Harmer, 1991)። Nunan (1989) እንደገለጹት፣ መጻፍ የስሜት ሕዋሳቶችን በማቀናጀት በርካታ ባህሪያትን በአንድ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ውስብስብ የአዕምሮ ስራ ነው ብለዋል። Byrne (1991) በበኩላቸው ጽህፈት የንግግር ድምፆችን የሚወክሉ ትዕምርቶችን በመጠቀም ሀሳብን በወረቀት ላይ የማስፈር ሂደት ነው ብለዋል።

የመጻፍ ክሂል እንደ ማዳመጥ እና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ሳይሆን መደበኛ ትምህርት ቤት በመማር የሚገኝ ክሂል ነው (Ondrakova፣ 2016)። በተመሳሳይም፣ አንድን ቋንቋ በመልመድ እና በመጠቀም ሂደት ውስጥ ጽህፈት ከማዳመጥ እና መናገር ክሂል ተከትሎ የሚመጣ ጉዳይ እንደሆነ (Park, 2004) ገልጸዋል። ጽህፈት በሌላም በኩል በመማር ብቻ የሚገኝ ክሂል እንደሆነም (Park, 2004) ጨምረው አስረድተዋል። እኚሁ ምሁር አያይዘው ሲገልጹም አንድን ቋንቋ በተገቢው እና በተሟላ መልኩ ለመልመድ ተማሪዎች ጽሁፍን በትምህርት ቤት ውስጥ እንደ አንድ ወሳኝ ክሂል ሊማሩት የግድ ይላል ብለዋል። Essa (2009) መጻፍን ሲገልጹ፣ የአንድ ቋንቋ ድምፆች በሚወክሏቸው ምልክቶች አማካኝነት ወረቀት ላይ የሚሰፍሩበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት ክሂል ነው ይሉታል። ይሁንና በማለት እኚሁ ምሁር፣ ጽሁፍ ለበርካታ ተማሪዎች ፈታኝ ነው ይላሉ።

ቀድሞ በነበረው ትምህርት ውስጥ ጽህፈት እንደ ሌሎቹ የቋንቋ ክሂሎች ትርጉም ትኩረት አግኝቶ የቆየ ሳይሆን ሰዋሠውን ለማስተማር ካለው ጠቀሜታ አንጻር ብቻ የሚታይ እንደነበር Leki and Richards (1990) ይገልጻሉ፡፡ ከጊዜ በኋላ የቋንቋ ዘርፍ ጥናቶች ሲበራከቱ፣ መጻፍ አንዱ የምርምር ትኩረት እየሆነ በመሄዱ ቀድሞ የነበረው አስተሳሰብ ላይ ለውጥ ይታይ ጀመር፡፡ በዚህም ጽህፈት የሰዋሰው ማስተማሪያ ብቻ ተደርጎ የመወሰዱ አስተሳሰብ እየቀረ አንድ ቋንቋ ክሂል መሆኑ ተቀባይነት አግኝቶ የትምህርትና የምርምር አካል ሆነ ሲሉ Weigle (2002) ይገልጻሉ፡፡ አያይዘውም ሲገልጹም፣ በቋንቋ ጥናት ውስጥ የተሳካ ትምህርታዊና ምርምራዊ ተግባራትን ለማከናወን ተፈላጊነቱ በመጨመሩ የቋንቋ ስርዓተ ትምህርት አካል ሆኖ እንዲሰጥ ምክንያት ሆነ በማለት Weigle (2002) ያስረዳሉ፡፡

ዛሬ ጽህፈት በየትኛውም የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይሰጣል (Park፣ 2004)፡፡ የመጻፍ ክሂል ካለው ፈታኝ ባህሪም አኳያም በመማር ሂደት ውስጥ በተማሪዎች የሚፈጸሙ በርካታ ስህተቶች መኖራቸውን Park፣ 2004) ገልጸዋል፡፡ በዚህም ችግሮቹን ለመለየት እና ለመፍታት የሚደረጉ ጥናቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መሄዳቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የጽሁፍ ችሎታን በማስተማር ሂደት ውስጥ በተማሪዎች የሚፈጸሙ በርካታ ስህተቶች እንደሚኖሩ የገለጹት (Ondrakova (2016)፣ የቋንቋ መማር ሂደት በመጀመሪያ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ምክንያት ስህተት ሊፈጠርበት ይችላል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም Ondrakova (2016) ሲገልጹ፣ አንዱ የማስተማር ሂደት ዓላማ ስህተት ማረም ነው፡፡ ቋንቋን በመማር ሂደት በተለይም በመጻፍ ክሂል ትምህርት ውስጥም ተማሪዎች ሲማሩ ስህተት ይፈጽማሉ፡፡ ስህተት በባህሪው የሚታረምና ተጨማሪ የመማር ሂደት ምክንያት ነው ብለዋል፡፡ እኚሁ ምሁር ሲገልጹ ስህተቶች የተጨማሪ ትምህርት አስፈላጊነትን መጠቆሚያ፣ ማነቃቂያ እና ለተማሪዎቸ መማርም ጠቃሚ ናቸው ብለዋል፡፡

ተማሪዎች ጽህፈትን ሲማሩ፣ አብዛኛዎቹ በተሰጠው ትምህርት ልክ ቢያንስ ዝቅተኛውን የመለኪያ መስፈርት የማያሟሉበት ጊዜ በርካታ ነው በማለት Norish (1993) ይገልጻሉ፡፡ Richards (1974) አያይዘው ሲያብራሩም፣ ቀላል የማይባሉ ተማሪዎች ጥሩ ጽሁፍ ሲጽፉ አይታዩም በማለት ለጽሁፍ ፍራቻ እና ጭንቀት የሚታይባቸው እንደሆኑም ገልጸዋል፡፡ የተማሪዎች የጽሁፍ ችግር በተለያዩ የትምህርት እርከኖች የሚስተዋል ቢሆንም፣ በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የክፍል ደረጃዎች ላይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ አድርጎታል ሲሉም Richards (1974) ጠቅሰዋል፡፡

በአጠቃላይ ጽህፈትን በተመለከተ የተለያዩ የዘርፉ ምሁራን ሲገልጹ በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶችን እንደሚፈጽሙ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ዙሪያ Norish (1993) ለአብነት ያህል ሲጠቅሱ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚማሩ ተማሪዎች የድርሰት አጻጻፍ ውስጥ በተደጋጋሚ ከሚታዩት ስህተቶች መካከል ከመደበኛው የቋንቋ ስርዓት ወጣ ያሉ መዋቅሮችን መጠቀም፣ የሚጽፉበትን ቋንቋ የጽሕፈት ህግ መሰረት አለማድረግ እና ተቀባይነት የሌላቸው የቃላት፣ የሆሄያት እና የዓረፍተ ነገር መዋቅሮችን እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል፡፡

ተማሪዎች ጽሁፍ ሲጽፉ ስለሚፈጽሙት ስህተት Goldstein (2005) ሲያስረዱ፣ በተለያዩ ምክንያቶች በመጀመሪያ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት፣ ከቋንቋ አጠቃቀም ችግር እና ከሠዋሰዋዊው ህግ ጋር ባለመተዋወቅ ምክንያት ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን ይፈጽማሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ Becker (2010) እና Gustilo (2011) እንደገለጹትም ተማሪዎች ባላቸው የተላያዩ የቋንቋው አጠቃቀም ዳራዎች የተነሳ ሲጽፉ ስህተቶችን ይፈጽማሉ ብለዋል፡፡

የተማሪዎችን የድርሰት አጻጻፍ ስህተቶች መሰረት (2003) በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የሚመደቡ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ የብቃት ስህተት ሲባሉ ሁለተኛዎቹ የችሎታ ማነስ ስህተት ናቸው፡፡ እንደ መሰረት (2003) ገልጻ በተማሪዎች የሚፈጸሙ የአፈጻፀም ስህተቶች የሆኑት የሆሄያት ግድፈቶች፣ የቃላት ድግግሞሻዊ አጠቃቀም፣ ሆሄያትን መድገም እና በጭማሪ መጠቀም የመሳሰሉትን ያጠቃልላሉ፡፡ እነዚህን ስህተቶች ተማሪዎች የሚፈጽሙት ቋንቋውን ሳያውቁ ቀርተው ሳይሆን በችኮላ፣ ትኩረት በማጣት፣ ባልተረጋጋ ስሜት፣ በጭንቀት ወይም በብስጭት ውስጥ ሆነው የሚጽፉት ጽሁፍ ነው፡፡

መሰረት (2003) የዕውቀት ማነስ ስህተቶችን ሲገልጹ፣ ተማሪው በተደጋጋሚ የሚፈጽማቸው እና በራሱ ማስተካከል የማይችላቸው እና በሌላ ሰው የእርምት እገዛ እስካልተደረገለት ድረስ ትክክል አድርጎቸው የሚቆጥራቸው ስህተቶች ናቸው (መሰረት፣ 2003)፡፡ ተመስገን ፈቀደ (2001) በበኩላቸው ከጽህፈት ክሂል ጋር ተያይዞ በሚፈፀሙ የተማሪዎች ስህተቶች ላይ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ከሰዋሰዋዊ ህግጋት አገባቡ ያለው አጠቃቀም ጋር ከስህተት እንዲጸዱ፣ በሳል የአጠቃቀም ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ተገቢ የቃላት አወቃቀሮችን እና የቋንቋ አጠቃቀሞችን በጥቅም ላይ ማዋል እንዲችሉ ትምህርት ሊሰጣቸው ይገባል ብለዋል፡፡

የመጻፍ ክሂል ትምህርት በኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው ቢሆንም እስካሁን የታለመለትን ግብ በሚጠበቀው መጠን ያሳካ ነው ለማለት ግን አይቻልም፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱ በ1951 ዓ.ም ተሻሽሎ ሲወጣ የትምህርት ዓይነቶቹ በውስጣቸው ሊይዟቸው የሚገቡ ይዘቶችን

አካቶ እንደነበር የአምላክስራ (2008) ይገልጻሉ፡፡ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከተካተቱት ይዘቶች መካከል አንዱ ደግሞ የድርሰት አጻጻፍ እንደነበር ትምህርት ሚኒስቴር፣ 1970ን ጠቅሰው የአምላክስራ (2008) ገልጸዋል፡፡
የጽህፈት ይዘቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያላቸውን ሚና በተመለከተ የተለያዩ አስረጅዎችን ባጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በማስከተል ደግሞ ይህ ጥናት ትኩረት ወደሚያደርግበት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር ከተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ማሻሻል ጋር ያለውን ትስስር በተለያዩ ምሁራን ወይም አጥኝዎች የተሰጡትን ሀሳቦች እንቃኛለን፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማዎች አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር ነው፡፡ ከእነዚህ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የመጻፍ ክሂል ነው፡፡ በመሆኑም የቋንቋ መምህራን የቋንቋን ትምህርት ዋና ዋና ዓላማዎችን ለማሳካት የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ይዘቶችን ተጠቅመው ማስተማር ተገቢ ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርትም ክሂሎችንና የእውቀት ዘርፎችን ለማስተማር ይዘቶችን በጽሁፎች አስደግፎ ያቀርባል፡፡ በመሆኑም አንድን የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ተከትሎ የቃላት፣ የሰዋሰው፣ የክሂሎችና የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ይቀርባሉ፡፡

Carter እና Long, (1991) ስነፅሁፋዊ አህዶች የዳበረ እውቀትን የሚወክሉ በመሆናቸው ክሂሎችን ያዳብራሉ፡፡ ለመምህራን የቋንቋ አጠቃቀሞችን (የቃላት ፍችዎችን፣ የዓረፍተ ነገር መዋቅሮችን፣ ቅደም ተከተሎችና የመሳሰሉትን) ለማስተማር ሲያገለግሉ፤ ለተማሪዎች ደግሞ የቃላት ዕውቀታቸውን ለማዳበርና ሃሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታቸውን ለማሳየት ይረዷቸዋል በማለት ገልፀዋል፡፡ እንደ Carter እና Long, (1991) አስተያየት በስነፅሁፋዊ አህዶች ማስተማር ክሂሎችን ለማዳበር ከማስቻሉም በላይ የተማሪዎችን ስሜት ስለሚማርክ በንቃት እንዲሳተፉና ትምህርቱን በጥሞና እንዲከታተሉ ያደርጋቸዋል፡፡ ከአዕምሮታዊ የዕውቀት ዘርፍ አንጻርም የቃላትና የዓረፍተ ነገር አወቃቀርና ይዘትን ለይቶ በመረዳት የመተንተን ዕውቀታቸውንና ችሎታቸውን ያዳብርላቸዋል፡፡

Hili (1986) ስነጽሑፍ ለቋንቋ ትምህርት የሚሆኑ አሀዶችን የመመጠን ችግር እንዳለበት በመጠቆም አሀዶችን መመጠን ተማሪዎች ቀጣይነት ባለውና እየጨመረ በሚሄድ መልኩ ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንዲማሩ ጥረት መደረግ ይኖርበታል፡፡ ይህም ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ለለመዱት ጽሑፍ እንዳይጋለጡ ያደርጋል፡፡

ስለሆነም እነዚህ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ እየተመረጡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ቢውሉ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ሊያሻሽሉ ይቻላሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለው ሚና ምን እንደሆነ መመርመር ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዋን ለጥናቱ ያነሳሳት ምክንያት በተከታታይ ለአስር ዓመታት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እያስተማረች ባለችበት ጊዜ ያስተዋለችው ችግር መኖሩ ነው፡፡ ይህም ችግር አጥኚዋ በመማር ማስተማር ሂደት እንዳስተዋለችው የሁለተኛ ደረጃ (9ኛ እና 10ኛ ክፍል) ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ ዐ.ነገሮችን በትክክል እንደማይጽፉ፣ የጽሁፍ መልመጃዎችን ለመስራት ፍላጎት እንደሌላቸው፣ የሚነበብላቸውን አዳምጠው ለመጻፍ ፍቃደኛ አለመሆናቸውን እና በፈተና ጊዜ በጽሁፍ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ባለመስራታቸው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑን በተደጋጋሚ ስታስተውል ቆይታለች፡፡

በመሆኑም የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ማነስ እንዴት ሊሻሻል ይችላል? የሚለው አጥኚዋን ሲያሳስባት የነበረ ጥያቄ በመሆኑ፣ ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከችግሩ አሳሳቢነት በመነሳት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማጎልበት የቋንቋ ትምህርቱ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቢሰጥ የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ሊሻሻል ይችላል የሚል መላምት ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ሀሳብ ለማረጋገጥ በፅኑ በመፈለጓ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡ በተጨማሪም አጥኚዋ ይዛው ከተነሳችው የጥናት መላምት ጋር የሚቀራረቡ ጥናቶችን ለመነሻነት ተመልክታለች፡፡

(Calvert, (2004) and Thom (2008)) ሲገልጹ ተማሪዎች ልብወለድ ፅሁፍ ሲያነቡ ከገፀባህሪያት ጋር የስሜት መጋራትን ይፈጥራሉ፡፡ ይህም በውስጣቸው የተጋሩትን ስሜት በቃላት፣ በዐ.ነገሮችና በአንቀፆች በፅሁፍ እንዲገልጹ በማድረግ ክሂሉን ማለማመድ ያስችላል ይላሉ፡፡ እንዲሁም (Hismongu, (2005) ቋንቋን በስነጽሁፍ ማስተማር በሚለው ጥናታቸው ተማሪዎችን መፃፍ ለማስተማር የገፀባህርያትን ማንነት በመጠቀም ያላቸውን አስተያየት በራሳቸው አገላለፅ እንዲፅፉ መርዳት ተመራጭ በመሆኑ ችሎታን ለማጎልበት የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመተግበር ክሂሉን ማዳበር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

Adiamy, (2011) እንደሚገልጹት የመፃፍ ክሂል አስቸጋሪ ተግባር ነው፡፡ አስቸጋሪነቱ የሚያሳየን ክሂሉ በድንገት የሚታወቅ ሳይሆን በበቂ ልምምድ የራስ የሚያደርጉት መሆኑን ነው፡፡ የተማሪዎችን የመፃፍ ፍራቻ ለመቀነስ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ማለማመድ ተገቢ ነው፡፡ ማረው (2003 ዓ.ም) በበኩላቸው "ተማሪዎችን የመፃፍ ክሂልን ለማለማመድ በሂደቱ ውስጥ ማለፋቸው አንድ ጉዳይ ቢሆንም ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ደግሞ የሚለማመዱባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት ነው" በማለት ገልፀዋል፡፡

Yavus, (2010) እንደሚያስረዱት የመጻፍ ክሂል የሚጽፉት ሀሳብ በማጣት ወይም የሚለማመዱበት ዘዴ ባለማግኘት ተማሪዎች ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም መምህሩ የተለያዩ ዘዴዎችን በማዘጋጀት እንደሌሎች ክሂሎች ያለ ጫና እንዲማሩት ማድረግ እንደሚጠበቅበት ይገልፃሉ፡፡

Graham, and Penn (2007) መጻፍን መማር እንደ አማራጭ የሚወሰድ ሳይሆን መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበራዊ ጉዳዮች ለመሳተፍም ሆነ በትምህርት ውጤታማ ለመሆን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መፃፍን ለማስተማርም አንድ የተወሰነ መንገድ ብቻ የለም ስለዚህ መምህሩ ተገቢ ነው የሚለውን የማስተማሪያ መንገድ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ እንደ ተመራማሪዎቹ አገላለጽ የመጻፍ ክሂልን ለማጎልበት የሚያስችሉ የተለያዩ መንገዶችን ተጠቅሞ ማስተማር አስፈላጊ ነው፡፡ እናም አጥኚዋ በትምህርት ቤቱ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የሚታየውን የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታና ፍላጎት ማነስን ለማሻሻል ትምህርቱ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቢሰጥ ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል ለመገምገም በመፈለጓ ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስታለች፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተጨባጭ ከመነሻው ለመጠቆም እንደሞከረችው በመማር ማስተማር ሂደት ያስተዋለችው የተማሪዎች የመጻፍ ችግር መኖርና ፍላጎት ማጣት ጥናቱን ለማካሄድ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት ሆኖዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንጻር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመጻፍ ፍላጎት ለማጎልበት ሌላም መንገድ ሊኖር ይችላል በሚል አነሳሽ ምክንያት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታን እና ፍላጎትን ሊያሻሽል ይችላል የሚል መላምት ለመንደፍ ችላለች፡፡ እናም ጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መላምት

- በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ጽህፈት የተማሩ ተማሪዎችየተሻለ የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት አላቸውን?
- በአጭር ልቦለድ ጽፈትን በተማሩና ባልተማሩ ተማሪዎች መካከል የጽህፈት ችሎታ ልዩነት የላቸውም፡፡

ጥናቱ እነዚህን መላምቶችለመመለስ የሚከተለውን ዓላማ ነድፎ ተግባራዊ አድርጓል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በዚህም የሚከተለውን ንዑስ አላማዎች ይዟል፡፡

### 1.4.1 ንዑስ አላማ

- በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ተጠቅሞ ጽህፈት ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታና የመማር ፍላጎትን ማሻሻል መቻሉን ማረጋገጥ
- በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ጽፈትን በተማሩና ባልተማሩ ተማሪዎች መካከል የመፃፍ ችሎታ ልዩነት መኖሩን መመርር ፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ለማስገኘት አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፡፡ለአማርኛ ቋንቋ መምህራንበአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ ከቃላት ምስረታ እስከ ሀሳብን በተሟላ ሁኔታ በፅሁፍ ለአንባቢ መግለፅን የሚሻሻልበትን ዘዴ ምላሽ ለማስገኘት ያስችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡የቋንቋ መምህራን የተማዎቻቸውን የመፃፍ ፍላጎት የሚያጎለብቱበትን ዘዴ ሊጠቁም ይችላል፡፡ለጥናት አድራጊዎችበስነጽሁፍ ይዘቶች ቋንቋን ማስተማር በተመለከተ ለሚነሱ ጥናቶች እንደ መነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና በሚል ርዕስ የሚጠና ነው፡፡ ጥናቱ በኦሮሚያ ክልል በጅማ ዞን በኦሞ ናዳ ወረዳ አሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም 10ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉትን ተማሪዎች የሚመለከት ነው፡፡ ቋንቋን ለማስተማር እንደ መሣሪያ የተጠቀመው የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ነው፡፡ አጭር ልቦለድ የተመረጠበት ምክንያት አንድን ሀሳብ፣ ጉዳይ እና ይዞ ስለተነሳው ርዕስ ነገር በመዘርዘር የመግለጽ ባህሪ ስላለው ነው፡፡ በዚህም የስነ-ጽሁፍ አሀድ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በጽህፈት ላይ ያለውን ሚና መርምሯል፡፡ ሌሎች ክሂሎች ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ ትኩረት አላደረገም፡፡ ስለሆነም በተጠቀሱት ነጥቦችና ምክንያቶች ጥናቱን ውስን ያደርገዋል፡፡

## 1.7 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

### 1.7.1 ያጋጠሙ ችግሮች

ይህን ጥናት ለማጥናት ስነሳ የሚከተሉትብ ችግሮች አጋጥመዋል፡፡

- ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸውአነስተኛ አመለካከት እና አንጠቀምበትም ቋንቋውን ከዚህ በኃላ ተፈላጊነትም የለውም የሚል እምነት በተማሪዎች ውስጥ በመኖሩ ምክንያት፡-
  1. ለሙከራ የተመረጡ ተማሪዎች ለቅድመ ፈተና ተሳታፊ መሆን አለመፈለግ ለትምህርት በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ሰዓቱን ጠብቆ አለመገኘት የድረ ፈተናውንም ለመፈተን አለመፈለግ፡፡
  2. ለሙከራ ቡድኑ የተዘጋጀውን የፅሁፍ መጠይቅ ለመሙላት ደስተኛ አለመሆንና በሰዓት አለመገኘት፡፡
  3. ለማስተማር የተመረጠው መምህር ለአበል የሚከፈለውን ገንዘብ ከበድ ያለ ዋጋን መጠየቁ፡፡

## 1.7.2 የተወሰዱ የመፍትሔ ሀሣቦች

1. ለሙከራ የተመረጡት ተማሪዎች ቅድመ ፈተናውን እንዲወስዱ/እንዲፈተኑ በትግስት በማግባባትና ትምህርቱን ቢማሩትም ዕውቀት እንደሚጨምርላቸውና ምንም አይነት ጉዳት እንደሌለውና መማር በራሱ እውቀት መጨመር መሆኑን ተማሪዎቹን በማሳመን ለማሳካት ተችሏል፡፡

2. የፅሁፍ መጠይቁን ለመሙላት በቀጠሮው ሰዓት ባይገኙም በሌላ ቀጠሮ ቀን በመቀየር እነሱ በሚመቻቸው ሰዓት በማካሄድ ተወጥተነዋል፡፡

3. ትምህርቱን ለማስተማር የተመረጠው መምህር ካለው የኑሮ ውድነት አንፃር ደስተኛ ባይሆንም በተቻለ መጠን በማግባባት ወደትግበራው እንዲገባ በማሳመን

# ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳናት

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመጻፍ ፍላጎት በማነሳሳት ረገድ ያለውን ሚና መፈተሽ ነው፡፡ ይህን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ለማብራራት በትኩረት ነጥቡ ዙሪያ ያሉ ተዛማጅ ጽሑፎችን ለመዳሰስና ትንታኔ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

### 2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝቶች

ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተመለከትነው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለው ሚና መመርመር ነው፡፡ በዚህ ክፍልም የመጻፍ ክሂል ምንነት፣ መጻፍን የማስተማር አስፈላጊነት፣ ስነጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ያለው ሚና፣ ስነጽሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት እና ምርምሩ የሚከተለው ስልት እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

#### 2.1.1 የመጻፍ ክሂል ምንነት

መጻፍ ማለት ሰዎች ለሰዎች የሚያቀርቡት ተግባቦታዊ ክንውን ነው፡፡ በመሆኑም የፀሀፊውና የአንባቢው ግንኙነት መልዕክትን የማስተላለፍና መልዕክትን የመቀበል ነው፡፡ በዚህም የቃላት ምርጫ፣ የሀሳብ አደረጃጀት፣ የአረፍተነገር ቅንብርን ሁሉ ያካትታል (Widowson, 1982)፡፡

የመፃፍ ክሂል ፊደላትን ከመፃፍ ጀምሮ ቃላትን መመስረት፣ ግልፅና የተሟላ ሀሳብን የያዙ አረፍተ ነገሮችን ማዋቀር፣ ተገቢ አያያዦችን በመጠቀም አንቀፅ ማደራጀት፣ ዘይቤዎችን በመጠቀም ተጠይቃዊ መልዕክት ያላቸው ፅሁፎችን ማቅረብ ነው (Venkates, 1987)፡፡

አንድ የተዋጣለት ፅሁፍ የሚባለው የቃላት አገባቡ፣ የአረፍተ ነገር መዋቅሩ፣ የአረፍተ ነገር ወሰኑ፣ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግ ተግባራዊ ማድረግ፣ የቃላት ምርጫው፣ ስርአተነጥብ አጠቃቀሙ፣ አንቀጽ ማደራጀቱ፣ ርዕስ መምረጡ፣ ሀሳብ ማፍለቁ ሁሉ ትኩረት የተሰጠው ከሆነ ነው (Raims 1983)፡፡

የመፃፍ ክሂል ሀሳብ ማደራጀትን፣ አንቀፅ መመስረትን፣ አረፍተ ነገር መመስረትን፣ የቃላት አመራረጥን፣ ስርአተነጥብ አጠቃቀምን እና የመሳሰሉትን ንዑስ ክሂሎች አካቶ የያዘ ነው (Adiamy, 2011)።

የመፃፍ ክሂል ተከታታይነት ያለው ልምምድ ካልተደረገ፣ ገንቢና ትምህርት ሰጭ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ካልተሰጠ፣ የመምህራን ክትትልና ድጋፍ ካልተደረገበት በሚፈለገው መልኩ ሊጎለብት አይችልም (Williams, 2003) እና (Zamel, 1982)። በተጨማሪም (Clark, 2003) የመፃፍ ክሂልን ለማጎልበት እና ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ ለማከናወን የመርህ ትምህርቱ አዘገጃጀት፣ የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ፣ የሚሰጠውም ምጋቤ ምላሽ፣ የምዘናና የግምገማ ስልቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንዳላቸው ገልፀዋል።

ከቀረበው የምሁራን ማብራሪያዎች የመፃፍ ክሂልን ምንነት እና ክሂሉ ሊጎለብት የሚችልባቸው መንገዶችን መረዳት ይቻላል። ይህም መፃፍ ተግባቦት እንደመሆኑ የቃላት ምርጫ፣ የአረፍተ ነገር መዋቅር፣ የስርአተነጥብ አጠቃቀም፣ ዘይቤያዊ አገላለፆች፣ የሀሳብ አፍልቆትና የመሳሰሉት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ትኩረት በማድረግና ግንዛቤ በማስጨበጥ የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ማጎልበት የሚቻል መሆኑን ነው።

## 2.1.2 መጻፍን ማስተማር አስፈላጊነት

የጽህፈት ትምህርት የተማሪዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። መምህራን ደስ ያላቸውን ርዕስ ለተማሪዎች በመስጠት ጽህፈትን ሲያስተምሩ ይስተዋላል። ሆኖም ተማሪዎችን ስለሚያውቁት ነገር ማጻፍ ጽህፈትንእጅግ አስቸጋሪ ተግባር እንደሆነ እንዲያስቡት ያደርጋቸዋል። ተማሪዎች ስለሚፈልጉት ርዕስ፣ በራሳቸው ቃላትና የአገላለፅ ችሎታ ተጠቅመው መጻፍን መለማመድ አለባቸው። መምህሩም ጽህፈት በአንድ ቅጽበት የሚከናወን ሳይሆን የተለያዩ ደረጃዎች በውስጡ የያዘ መሆኑን በመግለጽ ተማሪዎች እነዚያን ደረጃዎች ተከትለውእንዲለማመዱ ማድረግ አለባቸው (በድሉ 1996)።

Block and Mangiers (1995)ን በመጥቀስ በድሉ (1996) እንደተነተኑት ጥሩ የመጻፍ ችሎታ ተማሪዎች ጥሩ የማሰብ ብልሀት እንዲያዳብሩ ያደርጋል፣ መላ መምታትን፣ መጠየቅን፣ ግምት መስጠትን፣ መላምት ማረጋገጥንና የተደረሰበትን ውጤት መገምገምን እንዲማሩ ያደርጋል። አዘውትሮ የሚጽፍ ተማሪ የሚጽፈውን ይዘት እየከለሰ ይመረምራል፣ ያደራጃል። ተማሪው

ከቃላት ጋር ስለሚጫወት የተለያዩ ፍቺዎችን ያውቃል፣ የአገላለጽ ስልቱን ያዳብራል፣ የራሱን ሀሳብ ማደራጀት ይማራል።

እንደ በድሉ (1996) ትንተና ጽህፈት ሌሎች ክሂሎችን ማዳበር ያስችላል። ተማሪዎች በሚጽፉበት ጊዜ ሀሳባቸውን በተሻለ መንገድ ለመግለጽ ይፈልጋሉ። በጽሁፍ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ደጋግመው ያስባሉ፣ ይመረምራሉ። አግረመንገዳቸውንም ስለድርጊትና ቃላት ግንኙነት ይማራሉ።

እንደ Raims (1983) አገላለፅ ተማሪዎች ለምን እንደሚጽፉ በውል መገንዘብ፣ ለማን እንደሚጽፉ ለይተው ማወቅ፣ በተለያዩ ዘዴዎች መረጃ መሰብሰብና እንዴት መፃፍና ሀሳቦችን ማደራጀት እንዳለባቸው የስራ እቅድ ማውጣት ይገባቸዋል። ከዚያም መጀመሪያ ረቂቅ መንደፍ፣ መከለስ፣ የመጨረሻውን ፅሁፍ መፃፍና እንደገና በጥልቀት አንብቦ የመገምገም ሂደቶችን ማለፍ፣ የዐ.ነገር አደረጃጀቱ የተስተካከለ ፅሁፍ እንዲጽፉ ያስችላቸዋል። የመጻፍ ክሂልንም ማዳበር ያስችላል።

የመፃፍ ክሂል ከአፍላቂ ክሂሎች (Productive skills) አንዱ ነው። ይህ ክሂል ከጥቅም ላይ የሚውሉትን ፊደላት ቅርፃቸውን ጠብቆ ከመፃፍ ጀምሮ የተወሳሰቡ ሀሳቦችን በፅሁፍ እስከ መግለፅ ያሉትን ችሎታዎች ያካትታል። ይህ ክሂል ሀሳብን ለሌሎች ለማስተላለፍ፣ ትምህርትን ለመከታተልና ቋንቋን ለመማር የሚያስችል መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ስለሚችል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል (ማረው አለሙ 1998)።

በተጨማሪም Chaistan (1988) የመጻፍ ችሎታ ማደግ ያለበት መሰረታዊ የተግባቦት ክሂል በመሆኑና በየትኛውም የሙያ መስክ ተፈላጊ ክሂል ሲሆን፣ ለክሂሉ መዳበር የተሻለ የማስተማርያ ዘዴ መምረጥና የተማሪዎች ችሎታ እንዲዳብር ማገዝ የመምህር ድርሻ መሆኑን ገልጸዋል።

### 2.1.3 ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ያለው ሚና

ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ስነ-ጽሁፍ በየትኛውም የክፍል ደረጃ ለሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ተጨባጭ አውድ እንዲፈጠር አስፈላጊነቱ የላቀ ነው ብለው ምሁራን ይናገራሉ። ስነጽሁፍ በክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎችን በጥሩ ሁኔታ ለማሳተፍና

ሃሳባቸውን፣ ስሜታቸውን፣ ወዘተ እንዲገልጹ ለማመቻቸት ያግዛል። እናም ስነጽሁፍ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን፣ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### 2.1.3.1 ክሂልን ለማዳበር

ስነጽሁፍ ክሂሎችን ለማዳበር ቀላል የማይባል ድርሻ አለው። የስነጽሁፍ ስራ ሳቢ መሆኑ በተማሪዎች መካከል ባለው ውይይት የተሳታፊነት ደረጃቸውን ከፍ ያደርጋል። ተማሪዎች ተውኔት፣ ልቦለድ፣ ግጥም ወዘተ ሲያነቡ፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂላቸውን ያዳብራሉ። ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት መርጃነት መጠቀም የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ክሂል ያዳብራል፤ ምክንያቱም በነባራዊው ዓለም ላይ የተመሰረተና ታአማኒነት ያለው በመሆኑ ነው በማለት Ibsen (1995) ገልፀዋል።

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መካተት ያለባቸው የስነጽሁፍ አሀዶች ሙሁራን እንደሚገልጹት ተማሪዎችን ሊያሳትፉ የሚችሉና ሳቢ ከሆኑ፣ ክሂሎችን ለማዳበር ጉልህ ሚና እንዳላቸው መረዳት ይቻላል።

### 2.1.3.2 የአዕምሮ እድገትን ለማምጣት

በትምህርት ሊሰለጥኑ የሚችሉ ዋና ዋና የአዕምሮ ክፍሎች ቅንጅታዊ እድገት አስፈላጊ መረጃዎችን በማቅረብ ረገድ የስነጽሁፍ ስራዎች በትምህርት መስኮች የላቀ ድርሻ አላቸው። ከዚህም በተጨማሪ የተማሪዎችን ትጋትና ተነሳሽነትን ከፍ ያደርጋል በማለት በድሉ ዋቅጅራ (2007) ይገልጻል። ስነጽሁፍ የቋንቋ ክሂልን ከማዳበር ባሻገር የአዕምሮ እድገትን ለማምጣት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ሙሁራን ይገልጻሉ።

### 2.1.3.3 እውቀትን ለማዳበር

ስነጽሁፍ ስለሰውና ስለህይወት ያለንን እውቀት ከማስፋፋቱም በላይ አካባቢያችንን እና ማህበረሰባችንን ለመረዳት እንድንችል ያዘጋጀናል በማለት ዘሪሁን (1998) ያስረዳል። በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርቡት ስነጽሁፋዊ ይዘቶች መሰረታዊ የሆነውን ጉዳይ ማለትም የቋንቋ ክሂልን ለማሳደግ ነው። የቋንቋ ክሂል በለፀገ ማለት እውቀት የሚገኝበት፣ የሚፈለግበት፣ የሚግባባበት አቅጣጫ ሰፋለት ማለት ነው። እናም የቋንቋ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ የስነጽሁፍ ስራዎች ሲቀርቡ የተማሪዎች እውቀትም ይዳብራል ማለት ነው።

ከላይ የቀረቡትን ሀሳቦች የሚደግፉ በርካታ የዘርፉ አጥኝዎች ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Hill (1986), Brumfit and Carter (1986), Collie and Slater (1987), እና Lazar (1993) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ የሚያነሷቸው ነጥቦች፡- አንደኛ ስነጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ቀስቃሽ መሳሪያ ነው፤ ሁለተኛ ተማሪዎች የማህበር ባህላዊ ዕውቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ሶስተኛ ስነጽሁፍ የተማሪዎችን የቋንቋ ለመዳ ሂደት ያፋጥናል፤ አራተኛ ስነጽሁፍ የተማሪዎችን የቋንቋ እሳቤ ያሰፋል፤ አምስተኛ የተማሪዎችን የቋንቋ አተናተን (interpretation)ችሎታ ያዳብራል፤ ስድስተኛ ስነጽሁፍ የተማሪዎችን ሙሉ ስብዕና ለማዳበር ይረዳል የሚሉ ናቸው፡፡

## 2.1.4 ስነ-ጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት

### 2.1.4.1 ስነ-ጽሁፍ በእውነተኛ ቋንቋ የሚቀርብና ዋጋ ያለው መሆኑ

ስነጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና በተመለከተ Hill (1986) እንደገለጹት ስነጽሁፍ ቋንቋን የበለጠ ለመረዳት የሚረዳ፣ ስነልሳናዊ ትምህርት ግባትን በመፍጠር ሰፊ ንባብ ለማድረግ ያስችላል፡፡ እውነተኛ የቋንቋ አውድን በመፍጠር ተማሪዎች በራሳቸው ጥረት በቋንቋው የመግባባት አቅማቸው እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ በቋንቋው ውስጥ የተለያዩ ቅርጾች በማስገኘት ተማሪዎች ለትምህርቱ እንዲነሳሱ እድል ይፈጥርላቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከገለጻው መረዳት እንደሚቻለው የስነጽሁፍ ስራ በእውነተኛው አውድ መቅረብ ስለሚችል የተለያዩ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችና የቋንቋ ቅርጾችን የማሳየት አቅም አለው፡፡ ተማሪዎችም በቀረበው አውድ መሰረት የተለያዩ ተግባራትን መስራት ስለሚያስችላቸው በቋንቋው የመግባባት እድላቸውን ያሰፋዋል፡፡

### 2.1.4.2 ስነ-ጽሁፍ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለጸገ መሆኑ

ስነጽሁፍ የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ ሁነቶች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይንጸባረቁበታል፡፡ ልቦለዶች፣ አጫጭር ታሪኮች፣ ተውኔቶችና ግጥሞች የህብረተሰብን ባህል በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ፡፡ በተለይ ደግሞ ግጥም በተዘዋዋሪ መንገድ ከእውነታው ዓለም ጋር የተያያዘ ትርጉም እንዳለው Lazar (1993) (Weiddowson 1984)ን በመጥቀስ ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የስነጽሁፍ ስራዎችን በሚያነቡበት ጊዜ አውዳዊ እውቂያን ይፈጥርላቸዋል፣ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችንም ያስታውሳሉ በማለት Lazar (1993) ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ከ Lazar (1993) ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው፣ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በተለያዩ የስነጽሁፍ ዘሮች አማካይነት ይገለጣል ወይም ይተላለፋል፡፡ አንባቢ ባህልን በተለያየ መንገድ የሚያንጸባርቁ ልቦለዶችን፣ ታሪኮችን፣ ግጥሞችና ተውኔቶችን በሚያነብበት ጊዜ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ይገነዘባሉ፡፡ የባህል እውቂያን ይፈጥርለታል፡፡ የባህል እውቂያው በተራው የሚተላለፈውን መልዕክት አንባቢ በቀላሉ እንዲረዳው ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ስለባህል የሚያወሱ የስነጽሁፍ ዘሮች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውሉ ጠቀሜታቸው ዘርፈ ብዙ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

## 2.1.4.3 ስነ-ጽሁፍ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳድግ በመሆኑ

በቋንቋ ትምህርትክፍለ ጊዜ ውስጥ ስነጽሁፍን ከምንጠቀምባቸው ምክንያቶች አንዱ ተነሳሽነትን ማስገኘት መቻል ነው፡፡ ተማሪዎች አፍ በፈቱበት ቋንቋ ለስነ-ጽሁፍ እውቀት ቅርብ ከሆኑ፣ ቋንቋን እንደውጭ ወይም እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ ትምህርቱን ከራሳቸው ቋንቋ ጋር ለማዛመድ ይቀላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ስነጽሁፍ የእውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም መገለጫ በመሆኑ ትምህርቱ በስነጽሁፍ ይዘቶች አማካይነት ሲቀርብ ከራሳቸው ሕይወትና ልምድ ጋር በማመዛዘን የበለጠ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች ልቦለድን ሲያነቡ ከአዳዲስ ጭብጦችና አገላለጾች ጋር ተጋልጦ ይኖራቸዋል፡፡ በታሪኩም በመመሰጥ በተነሳሽነት ስሜት እንዲያነቡ ያስችላቸዋል በማለት (Lazar 1993) ያስረዳሉ፡፡

እዚህ ላይ ለመግለጽ የተፈለገው መሠረታዊ ጉዳይ በቋንቋ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ስነ-ጽሁፍን መጠቀም መነሳሳት እንዴት ሊከሰት ይችላል የሚለው ነው፡፡ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስለሚንፀባረቅባቸው ተማሪዎች ከሕይወት ገጠመኞቻቸው ጋር በማስተሳሰር ማብራሪያ ይሰጣሉ ማለትም ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች አጫጭር ትረካዎችን፣ ልቦለዶችን ሲያነቡ አዳዲስ ጭብጦችንና አገላለጾችን ሊያገኙ ስለሚችሉ፣ በተነሳሽነት በንባባቸው ይገፋሉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

ዘመንፈስ (1991) "በስነ-ጽሁፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና" በሚል አጥንተዋል፡፡ በዚህ ስራቸው ኢብሰን (1995)ን ጠቅሰው እንደገለጹት ስነጽሁፍን እንደመሳሪያነት ተጠቅሞ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ሊገኝ የሚችለውን ጠቀሜታ በሁለት መንገድ መግለፅ ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የስነጽሁፍ ሚና እሙናዊ (Authentic) በመሆኑ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ የቋንቋ መማር ሂደት ያፋጥናል፡፡ በዚህ በኩል በተለይ ስነጽሁፋዊ

አህዶች (Literary texts) የዳበረ ዕውቀትን የሚወክሉ በመሆናቸውና የስነጽሁፍ መለያ ባህሪውም አሻሚ ስለሆነ፣ ጽሁፍን (አህዱን) ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች በመካከላቸው የተለያዩ አስተያየቶችንና ግንዛቤዎችን ይፈጥራሉ። የጽሁፉን አሻሚነት ለመረዳት በሚደረገው ጥረትም አንባቢውን ሊስቡ የሚችሉ ብዙ አከራካሪና አወያይ ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። በዚህም ምክንያት የአንባቢው ምላሽ በአህዱ ውስጥ ከሰፈረው ሀሳብ ጋር ባለመስማማት የሚከተለው ክርክር ጥሩ የክፍል ውስጥ መልመጃ ይፈጥራል። በስነጽሁፍ ዓለም ልምድን ከፈጠራ ጽሁፎች ጋር ለማዛመድ በሚደረገው ጥረት "ትክክለኛ" ነው ተብሎ የሚገመት መፍትሔ ስለሌለ፣ በዚህ ምክንያት በክፍል ውስጥ በሚነሳ ውይይት ጥሩ የሆነ ተግባቦትን ይፈጥራል።

ዘመንፈስ (1991) በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሱት ጠቀሜታ ከዓላማው አንፃር ሲታይ ከዕውቀት ጋር የተያያዘ ነው። ስነጽሁፍን ማንበብ፣ብሎም ስለሱ መናገርና መፃፍ ቋንቋን በመማር ረገድ ስሜታዊ (Affective) እና አዕምሮታዊ (Cognitive) ሂደትን የተከተለ ነው። ስሜታዊ የዕውቀት ዘርፍ፣ አንባቢ ከስነጽሁፍ ጋር ተገናኝቶ የግል ስሜቱንና ተሞክሮውን እንዲያንፀባርቅ ዕድል ይሰጠዋል። በዚህም ምክንያት አንድ ተማሪ ስለራሱ ብዙ ሊገነዘብበትአልያም ቀደም ብሎ ከሚያውቀው ማህበራዊ ሁኔታ ጋር እንዲያነፃፅር ያስችለዋል። በዚህም የተነሳ ተማሪው ስሜቱ ስለሚማረክ በቋንቋው ትምህርት እንዲሳተፍና ትምህርቱንም በጥሞና እንዲከታተል ያግዘዋል። በአዕምሮታዊ የዕውቀት ዘርፍም የቃላትና የአረፍተ ነገር ቅርፅንና መዋቅርን፣ የዲስኩር ስድሮችን (Discourse paterns) እና ይዘቶችን (Content) ለይቶ ለማወቅ የቋንቋ ትንተና (Interpretation) ዕውቀቱንና ችሎታውን የሚያዳብርበት ነው። ተማሪው በእንደዚህ ሁኔታ ከፈጠራ ጽሁፎች ጋር በሚተዋወቅበት ጊዜ የቋንቋ አጠቃቀም ፈሊጥ በቋንቋ የሚገለፅበት ሁኔት እንዳለ ጭምር የሚረዳበት ነው።

## 2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ማህቀፍ

Hill (1986) እንዳብራሩት ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማካተት ለተማሪዎች ጠቅላላ እውቀት፣ አእምሯዊ ብስለት፣ ማህበራዊና ስነምግባራዊ እድገት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር እውነተኛ አውድን ስለሚፈጥርና ተማሪዎችን ስለሚያሳትፍ የቋንቋውን ትምህርት የተሳካ ያደርገዋል። ሆኖም ግን ይህንን ማሳካት ይቻል ዘንድ Carter and Long, (1991) ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለማካተት በቅድሚያ "ስነጽሁፍ ለምን?" የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ መመለስ ጠቃሚ መሆኑን ይገልጻሉ።

Carter and Long, (1991)፣ Lazar (1993) እና Brumfi and Carter, (1986) እንደሚያስገነዝቡት ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ለማካተት ያስፈለገበት ምክንያት የሶስት የማስተማሪያ ሞዴሎችን ዓላማ ግብ ለማሳካት ሲባል ነው፡፡ እነሱም ባህላዊ ሞዴል የቋንቋ ተኮር ሞዴልና የስብዕና ግንባታ ሞዴል (Personal development / enrichment) ሲሆኑ ሶስቱም የየራሳቸው ዓላማ፣ የማስተማሪያ ዘዴና የተግባር ልምምድ ያላቸው ናቸው፡፡

የመጀመሪያው በባህላዊ ሞዴል መሰረት ስነጽሁፍን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት ስነጽሁፍ የሰዎችን ሀሳብና ስሜት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር በስነጽሁፍ አማካኝነት ቋንቋን ማስተማር በዘመናት የተንጸባረቁ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ለሰው ልጆች ትልቅ ዋጋና ሁለንተናዊ እሴቶች ያሏቸው ባህላዊ ሀብቶችን ተማሪዎች እንዲያገኙ ማስቻል ነው (Carter and Long, 1991)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም Collie, and Slater (1987) እንደሚያብራሩት ተማሪዎች የስነጽሁፍ አሀዶችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ባደገ መጠን እርካታን በማግኘት ለበለጠ ንባብ ይነሳሳሉ፡፡ በዚህም ሂደት ውስብስብ ባህላዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ማድነቅና መተቸትን ይማራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ ባህልና ራሳቸውን በትኩረት እንዲመለከቱ፣ እንዲመረምሩና እንዲረዱ ያነቃቃቸዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የስነጽሁፍ አሀዶችን እንዲያነቡ ማበረታታትና ማገዝ ማለት ስነጽሁፋዊ አሀዶቹ የተጻፉበትን አካባቢና ማህበረሰብ አጠቃላይ ገጽታዎችን እንዲረዱ ማገዝ ነው፡፡

ሁለተኛው ቋንቋ ተኮር ሞዴል ሲሆን Lazar (1993) እንደሚሉት የዚህ ሞዴል አጠቃላይ እሳቤው በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ቋንቋና ስነጽሁፍን አዋህዶ በማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ መማር ዓላማ (ዎች)፣ የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀቶችን ለማዳበር ያስችላል የሚል ነው፡፡በመሆኑም በቋንቋ ተኮርሞዴል ስነጽሁፍን ማጥናት ሳይሆን አሀዱን ለተከታታይ የቋንቋ ተግባራት እንደምንጭ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም ስነጽሁፍ በቋንቋ ክፍል ውስጥ ከፍተኛ መነቃቃትን ስለሚፈጥርና የሰው ልጆችን የህይወት ልምድና ገጠመኝ በማቅረብ የተማሪዎችን ትኩረት ስለሚስብ ተማሪዎች በራሳቸው ቋንቋ ከተፃፈ ስነጽሁፍ ጋር ከተዋወቁ በኋላ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚቀርቡ አሀዶችን በንፅፅር ለማጥናት ይበረታታሉ፡፡ ይህም ተማሪዎችን ውስብስብ ለሆነ የቋንቋ አገልግሎት በማጋለጥ ለአዲስና ከግምት በላይ ለሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ያበቃቸዋል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ ለውስብስብ ጭብጥ እንዲጋለጡ በማድረግ ያልተለመደ የቋንቋ አጠቃቀምን እንዲረዱ ማድረግ ተገቢ መሆኑን Lazar (1993) አክለው ገልፀዋል፡፡

ሶስተኛው ስነጽሁፍን ማስተማሪያ ሞዴል የስብዕና ግንባታ ሞዴል ነው፡፡ በዚህ ሞዴል ስነጽሁፍን የማስተማር አስፈላጊነቱ የስነጽሁፍ ፈተናን እንዲያልፉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን የተማሪዎችን ስብዕና ማደራጀት ወይም ማዳበር ነው፡፡ የመምህሩ ተግባርም የተማሪዎችን ስብዕና የሚያጎለብቱ የስነጽሁፍ አህዶችን በመምረጥ ተማሪዎች በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በንባብ እንዲጠመዱ በማድረግ የንባብ ፍላጎታቸውንና ዝንባሌያቸውን እንዲያሳድጉ ማነቃቃትና መርዳት ነው (Carter and Long, 1991)፡፡

እንደ Collie, እና Slater (1987) ማብራሪያ ስነጽሁፍ የቋንቋን የተለያዩ ተግባራት ለተማሪዎች ያቀርባል፡፡ ተማሪዎች ጥልቅና አውዳዊ አህዶችን በማንበብ ከበርካታ ምንባቦችና የአህድ አውድ ገፅታዎች ጋር እንዲለማመዱ ያደርጋል፤ የአረፍተ ነገሮችን አመሰራረት ተግባርና የተለያዩ የሀሳብ ማያያዣ መንገዶች ያቀርባሉ፤ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ክለሳ ድርሳናት ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት የሶስት የማስተማሪያ ሞዴሎችን ዓላማ ግብ ለማሳካት እንደ ሆነ ይገልጻሉ፡፡ እነሱም ባህላዊ ሞዴል፣ የቋንቋ ተኮር ሞዴልና የስብዕና ግንባታ ሞዴል (Personal development / enrichment) ናቸው፡፡ ከነዚህ ሞዴሎች ውስጥም የቋንቋ ተኮር ሞዴል በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ቋንቋና ስነጽሁፍን አዋህዶ በማስተማር የተማሪዎችን የቋንቋ መማር ዓላማዎችን፣ የቋንቋ ክሂሎችንና እውቀቶችን ለማዳበር የሚያስችል በመሆኑ ጥናቱ ይሄን ሞዴል ይከተላል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ማሻሻልና የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለው ሚና ላይ ያተኩራል፡፡

Carter and Long, (1991) የቋንቋ ሞዴል በማስተማሪያ ክፍል ውስጥ በብዛት የተለመደ አቀራረብ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ ይኸውም፡-

- በቋንቋ እና ስነጽሁፍ መካከል ጥብቅ ትስስር ይፈልጋል፤
- ተማሪዎች የቋንቋ ብቃታቸውን ማሻሻል ይችላል፤
- በቋንቋ ማስተማር ላይ ስነ-ጽሁፍን በምንጭነት ይጠቀማል፤
- ተማሪዎች በአህድ (text) ውስጥ ተሳትፎ አላቸው፤
- ለስነ-ልሳን ልምምድ ያነሳሳል፤

- ተከታታይ የቋንቋ ተግባራትን ያቀርባል።

Carter (1988) የቋንቋ ሞዴል፡-

- በቋንቋ እና በስነ-ጽሁፍ መካከል ትልቅ ተዋህዶ ይፈልጋል፤
- ተማሪዎች በቋንቋው አጠቃቀም ላይ እንዲያተኩሩ ያግዛቸዋል፤
- የስነ-ጽሁፍ ስራዎችን የቋንቋ መልመጃ ምንጭ አድርጎ ይመለከታል፤
- ስነ-ጽሁፍን እውነታንና መረጃን ለማግኘት ከማጥናት ይልቅ በተከታታይ ለቋንቋ ተግባራት ያቀርባል፤
- በብዛት ተማሪ ተኮር የመሆን አላማ አለው፤
- ዋና ትኩረቱ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ነው፤
- የትኩረት አቅጣጫ መምረጥ ይችላል፤
- ስልታዊ አተናተን ይከተላል፤

በማለት የቋንቋ ሞዴል ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት እንደመሳሪያነት የመጠቀም ዓላማ በቋንቋ ክሂሎች ልምምድና እውቀት ላይ የሚያተኩር መሆኑን ይገልጻል።

## 2.3 የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

በዚህ ክፍል የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዛው ከተነሳችው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ሊመሳሰሉ የሚችሉ ስራዎችን ለመቃኘት ሞክራለች። ቅኝቱ መሰረት ያደረገባቸው ነጥቦችም ከጥናት ርዕስ፣ ከጥናት አካላዮች፣ ከጥናት ዘዴዎች፣ ከጥናት ትኩረትና ከጥናት ውጤቶች አንጻር አንድነትና ልዩነታቸውን በመዳሰስ ነው። ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ግንኙነት ያላቸው በሀገር ውስጥ ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ የዘመንፈስ (1991) እና የፀጋየ (2004)፣ ጥናት ይጠቀሳሉ።

የዘመንፈስ (1991) "በስነጽሁፍ አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና" በሚል ርዕስ ላይ ጥናት አካሂደዋል። የጥናቱ ዓላማ በስነጽሁፍ አማካኝነት ቋንቋን በማስተማር ረገድ የአጭር ልቦለድ ሚናን መፈተሽ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በየካቲት 12 ትምህርት ቤት የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን፤ የጥናቱ ዋና ትኩረት በአጭር ልቦለድ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር አባይት እና ንኡሳን ክሂሎችን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው በጥብቅና የሙከራ ሁለት ቡድኖች ላይ ነው። ሁለቱ

ቡድኖች ቅድመ ትምህርት ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት ግን ልዩነት ያልታየበት ሲሆን፤ በተለያየ ዘዴ ከተማሩ በኋላ ተፈትነው ያስመዘገቡት ውጤት ግን ልዩነት ያለው መሆኑ ተገልጿል፡፡ በአጭር ልቦለድ የተማሩት በተለመደው ዘዴ ከተማሩት ቡድኖች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ከጥናቱ ውጤት መረዳት እንደሚቻለው በቋንቋ ትምህርት የስነጽሁፍ አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡እናም ስነጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀሙ እና በዘዴው ከአጥኚው ጥናት ጋር ይመሳሰላል፡፡ ይሁን እንጂ የዘመንፈስ (1991) ጥናት ዋና ትኩረቱ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት አጭር ልቦለድ እየሰጠ ያለውን ፋይዳ መመርመር በመሆኑና የመጻፍ ክሂልን በማጎልበት ረገድ ያለውን ፋይዳ በጥልቀት ባለማሳየቱ ከዚህኛው ጥናት ጋር ይለያል፡፡

አጥኚዋ ለማሳየት የምትሞክረው የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ለማስተማሪያነት በመጠቀም የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂልና ፍላጎት ለማጎልበት የሚሰጠውን ፋይዳ መመርመር ይሆናል፡፡

ፀጋየ (2004) "የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ተማሪዎች የስነጽሁፍ ቴክስቶችን ለቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ ስለመጠቀም ያላቸው አመለካከትና የክፍል ውስጥ አተገባበር" በሚል የሰሩት የምርምር ጥናት ሲሆን ጥናቱ የተካሄደው ገላጭ ንጽጽራዊ የምርምር ስልትን ተከትሎ ነው፡፡ የተገኘው ውጤትም ስነጽሁፋዊ ቴክስቶችን በክፍል ውስጥ ስለመጠቀም በመምህራንና በተማሪዎች አተገባበር ልዩነት ታይቷል የሚል ነው፡፡ የመምህራን አተገባበር ከተማሪዎች አተገባበር የበለጠ እንደሆነ ገልጸው ይህም ሊሆን የቻለው ለቋንቋው ማስተማሪያነት የሚቀርቡትን ስነጽሁፋዊ ቴክስቶች ተግባራት በብዛት የሚያከናውኑት መምህራንበመሆናቸው የመጣ መሆኑን በጥናታቸው ጠቁመዋል፡፡ ይህ ጥናት የስነጽሁፍ ቴክስቶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን በመጥቀስ በክፍል ውስጥ በአተገባበር ላይ በመምህራንና በተማሪዎች መካከል ልዩነት እንዳለ እና መምህራን ከተማሪዎች የበለጠ ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ያመለክታል፡፡ ይሁንና ከዚህኛው ጥናት ጋር የስነጽሁፍ ቴክስቶችን ለቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ በመጠቀም ተመሳሳይነት ሲኖረው በትኩረቱ ላይ እና በጥናቱ ዘዴ ልዩነት አለው፡፡

እነዚህ የሀገር ውስጥ ጥናቶች ስነጽሁፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከመጠቀም ጋር በተያያዘ የተሰሩ በመሆናቸው ከዚህኛው ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ ይሁንና የሁለቱም ጥናቶች የትኩረት ነጥብ ከአጥኚዋ ጥናት ይለያል፡፡ የዘመንፈስ በአዲስ አበባ የተካሄደ ጥናት ሲሆን፣ ትኩረቱ አጭር ልቦለድ ቋንቋን በማስተማር ረገድ ያለው ሚና ላይ ነው፡፡ የፀጋየ ደግሞ ስነጽሁፋዊ

ቴክስቶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም ላይ የመምህራንና የተማሪዎች አመለካከትና የክፍል ውስጥ ትግበራ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡

ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ ግንኙነት ያላቸው በውጭ ሀገር ከተሰሩ ጥናቶች ውስጥ የ Yeasmin, (2011) እና የ Ahmed Sallal, (2014) ጥናት ይጠቀሳሉ፡፡ Yeasmin (2011) የጥናቱ ዓላማ ስነ-ጽሁፍ በቋንቋ ትምህርት ያለውን ውጤታማነት ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ መሰረት ያደረገው በብሪታኒያ መማክርት "የአንባቢዎች እድገት ፕሮግራም" የሚለውን አቅጣጫ የተከተለ ነው፡፡ ጥናቱ የተሰራው በባንግላዲሽ ነው፡፡ ጥናቱ በዓላማው መሰረት በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር መካከል ያለውን የክርክርና ስምምነት ሁኔታ ይመረምራል፡፡ በስነጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ አጫጭር ልቦለዶች የዘመኑን ሁኔታ የሚገልጹ ተማሪዎች የተለያዩ ውይይቶች፣ ክርክሮች፣ ግለ ገለጻዎች እንዲያደርጉ የሚያነሳሱ መሆናቸው፣ በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን ለማዘጋጀት እንደሚያስችል አብራርቷል፡፡ ስለሆነም ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ የስነጽሁፍ ይዘቶች ተመርጠው መዘጋጀት እንዳለባቸው አሳስቧል፡፡

ከተሰጠው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው፣ ስነ-ጽሁፍ በተማሪዎች ላይ የዘላቂ አንባቢነት ተግባርን ለማሳደግ እንደሚያስችል፣ እንዲሁም ተማሪዎች የውይይት፣ የክርክር፣ ሀሳብን የመግለጽ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያስችላቸዋል፡፡ ይህ ጥናት፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዛው ከተነሳችው የማስተማር ዘዴ ጋር ተመሳሳይነት አለው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በሁለቱም ጥናት ተተኳሪዎቹ በስነጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ነው፡፡ ይሁን እንጂ መሰረታዊ ዓላማው ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ጋር የተሳሰረ ሲሆን ይሄኛው ግን ከመጻፍ ችሎታ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ ይለያያል፡፡ እንዲሁም የዚህ ጥናት አቅራቢ ከስነጽሁፍ ዘርፎች፣ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢን ለማስተማሪያነት በመጠቀም በተማሪዎች ላይ ሊመጣ የሚችለውን የመጻፍ ችሎታ ለውጥ የሚፈትሽ በመሆኑ የተለየ ያደርገዋል ማለት የቻላል፡፡

Ahmed, Sallal, (2014) ያጠኑት ደግሞ አጫጭር ትረካዎች በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያላቸውን ሚና መለየት በሚል ዓላማ ነው፡፡ እንዲሁም አጫጭር ትረካዎች የንባብ ስሜትን የመቀስቀስ ሚና ምንያህል እንደሆነ ለመለየት ጥረት ተደረጓል፡፡ ጥናቱ በቁጥጥርና በሙከራ ቡድኖች የተከፈለ ሲሆን ለሙከራ ቡድኑ በአጫጭር ትረካዎች የታገዘ ትምህርት ሲሰጥ፣ ለቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደው መንገድ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም የአንብቦ መረዳት ችሎታን እና የማንበብ ተነሳሽነትን የሚመዝኑ ጥያቄዎች ተፈትነዋል፡፡ በዚህም

መሰረት በአጫጭር ትረካዎች የተማሩ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ተሻሽሏል፤ ተነሳሽነታቸውም ጨምሯል፡፡ የሚሉ ማጠቃለያዎች ላይ መደረሱን ያስገነዝባሉ፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተጠቀመችው የአጭር ልቦለዶችን ቅንጫቢዎች ሲሆን፣ Ahmed, Sallal, (2014) ደግሞ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተጠቀሙት አጫጭር ትረካዎችን ነው፡፡ በዚህም ልዩነት እንዳለው መገንዘብ ቢቻልም፤ በጥናቱ ዘዴ ግን ተመሳሳይነት አለው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም በራሷ አካባቢ በተማሪዎች ላይ ሊመጣ የሚችለውን የመጻፍ ችሎታ መሻሻል ለመፈተሽ ያስችላታል ማለት ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

### 3.1 የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት የሚከተለው የአጠናን ዓይነት ቅይጥ ሲሆን ከፊል ሙከራዊ (experimental) የምርምር ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ነው፡፡ በዚህ የምርምር ስልት መሰረት ቅድመ ሙከራዊ (per-experimental) ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ተላውጦዎችን በተመለከተ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢን ተጠቅመዉ እና በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ሳይጠቀሙ ቋንቋን ማስተማር ነፃ ተላውጦ ሲሆን፣ የመጻፍ ችሎታ እና የመጻፍ ፍላጎት ጥገኛ ተላውጦዎች ናቸው፡፡ ጥናቱ ሁለት የጥናት ተሳታፊ ቡድኖች የቁጥጥር እና የሙከራ (Control and Experimental) ያሉት ሲሆን በጥናቱ ለተሳተፉ ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርት ፈተናና የድህረ-ትምህርት ፈተና (per-test and post-test)ተሰጥቷል፡፡ በጥናቱ ተሳታፊ ለሆኑ ተማሪዎች የክፍል ደረጃውን መማሪያ መጽሐፍ መሰረት የሚያደርግ የትምህርት ይዘት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ሳይማሩና በቅንጫቢው ከተማሩ በኋላ በተማሪዎች ላይ የሚታየውን ለውጥ ተመርምሯል፡፡ የፈተናና የፅሁፍ መጠይቅ ውጤት በመተንተን የሚደረስበት ማጠቃለያም ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

### 3.2 የጥናቱ አካላይ

ጥናቱ የተከለለው በኦሞ ናዳ ወረዳ ውስጥ ያሉ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ እነዚህም፡- የአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የናዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የአሌ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የቦነያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና የኢፈ ቦሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ ተመርጧል፡፡

### 3.3 የጥናቱ ቦታ (ትምህርት ቤት) አመራረጥ

የአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኦሞ ናዳ ወረዳ ካሉ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ አንዱ ሲሆን በትምህርት ቤቱ በ2015 ዓ.ም ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ወንድ 947 ሴት 1059 ድምር 2006 ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ የትምህርት ቤቱ አመራረጥ በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ምክንያቱም አጥኚዋ በዚያው ትምህርት ቤት እያስተማረች መሆኗና ሙከራዊ ጥናቱን በቅርበት የመከታተልና የመማር

ማስተማር ሁኔታውን ለመመልከት፣ የመፈተን ተግባር ለማከናወን ስለሚመች ነው፡፡ አመቺ ናሙና አመራረጥ አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ ነው ብላ ያመነችበት በአመቺ ይመረጣል ያለው (2004) በማለት ያስረዳል፡፡ ከተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለጥናቱ አስተዋፅኦ ለሚያደርጉ አካላት የምርምሩን ዓላማ በማስረዳት ይሁንታን ለማግኘት ሞክራለች፡፡

## 3.4 የተማሪዎች እና የመምህራን ናሙና አመራረጥ

የአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍልን አንድ ላይ የያዘ ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጡት በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በ2015 ዓ.ም 10ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ናቸው፡፡

በትምህርት ቤቱ 10ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉትን ተማሪዎች በመመልከትና ከሰነዶች በተረጋገጠው መሰረት 316 ወንዶች እና 271 ሴቶች በጠቅላላ 587 ተማሪዎች በስምንት መማሪያ ክፍሎች ተደልድለው ይገኛሉ፡፡ በአንድ መማሪያ ክፍል ደግሞ በአማካይ 73 ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ጥናቱ በከፊል ሙከራዊ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ማድረግ አልተቻለም፡፡ ስለዚህም አጥኚዋ ተማሪዎቹ የተመደቡት በችሎታ ስብጥር መሆኑና የአንደኛው ወሰነ ትምህርት አማካይ ውጤታቸው ተቀራራቢ መሆኑን ከውጤት ትንተና መዝገብ ካረጋገጠች በኋላ በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች (10ኛ"B" እና 10ኛ"D")ተመርጠዋል፡፡ ከነዚህ ሁለትክፍሎች መካከል ደግሞ በእድል ሰጭ ናሙና ዘዴ በመጠቀም10ኛ"B" የሙከራ እና 10ኛ"D" የቁጥጥር ቡድን በማለት ተመድበዋል፡፡ለሙከራ ቡድኑ ከተመረጡት ክፍል ተማሪዎች በቅድመ ፈተና የተሻለ ዉጤት ያመጡትን 32 ተማሪዎች የጥናቱ ቡድን በመሆን ተወስደዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የቁጥጥር ቡድን በተለመደው መንገድ ነፃው ቡድን ደግሞ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች እንዲማሩ በማድረግ ለጥናቱ ተመርጠዋል፡፡

በትምህርት ቤቱ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ያሉ ሲሆን፣ እያንዳንዳቸው የተለያየ የክፍል ደረጃን ያስተምራሉ፡፡ከአራቱ መምህራን 10ኛ ክፍል የሚያስተምረውን መምህር በአመቺ የናሙና አመራረጥ ዘዴ በተጠኝነት በመምረጥ ተጠኝ ተማሪዎችን እንዲያስተምር ተደርጓል፡፡ ይኸውም ጥናቱ 10ኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎችን የሚመለከት በመሆኑ ለመማር ማስተማሩ ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ታስቦ ነው፡፡

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ለጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጡ ዘዴዎች ፈተና እና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ቅድመ-ልምምድና ድህረ-ልምምድ የጽሁፍ ችሎታን ያካተቱ ፈተናዎች እና በልምምድ ጊዜ የተማሪዎችን ሁኔታ መሰረት የሚያደርግ የጽሁፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### 3.5.1 ፈተና

በዚህ ጥናት በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግለው ፈተና ነው፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ በጥናቱ የሚሳተፉ ተማሪዎች አንድ ፈተና በቅድመ-ትምህርት እና አንድ ፈተና በድህረ-ትምህርት (ከልምምድ) በኋላ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

የፈተና ዝግጅት አላማን ያለው (2004) እንደገለጹት ፈተና የሚዘጋጀው የተፈታኞችን እውቀት፣ ችሎታ እና ፍላጎት አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚሆን፣ በጥናቱ የቅድመ-ትምህርት ፈተና አላማ ተደርጎ የተዘጋጀው የጥናቱ ተሳታፊዎች ወደ ትምህርቱ ከመግባታቸው በፊት የሚኖራቸውን የመጻፍ ችሎታ ለመፈተሽ ሲሆን፣ የድህረ-ትምህርት ፈተናው የተዘጋጀው የጥናቱ ተሳታፊዎች ከትምህርቱ (ከልምምዱ) በኋላ የሚያሳዩትን የመጻፍ ችሎታ መሻሻል ለመገምገም ነው፡፡ የፈተናው ዝግጅት፣ የቅድመም ሆነ የድህረ ፈተና ጥያቄዎች በቁጥርም ሆነ በይዘት ተመሳሳይ ሲሆን የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለመለካት የቋንቋና የስርአተ ነጥብ አጠቃቀማቸውን፣ የርዕሱን ይዘት በተገቢ ሁኔታ መግለፃቸውን፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀራቸውን፣ የአንቀፅ አደረጃጀታቸውን የሚለኩ ሆነው መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ስለዚህ ፈተናዎቹ የክፍል ደረጃውን መማሪያ መጽሀፍ መሰረት አድርገው በአጥኚዋ ከተዘጋጁ በኋላ ለተማሪዎች ደረጃ የሚመጥኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአጥኚዋ አማካሪና ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋን በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተገምግሞ በሚሰጥ አስተያየት ተስተካክለው ቀርበዋል፡፡

እነዚህ ሁለት ፈተናዎች የጥናቱ ዋና መረጃ መሰብሰቢያ ሆነው ሲዘጋጁ፣ እያንዳቸው አንድ አንድ ምንባብ ኖሯቸው በስራቸው ደግሞ ሃያ ሃያ ጥያቄዎችን አካተው ይዘዋል፡፡ ጥያቄዎቹ ሦስት ክፍል አላቸው፡፡ በሦስቱ ክፍሎች የተለያየ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ መፃፍን ማስተማር ለመፃፍ ክሂል እና ፍላጎት መዳበር ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳለው ለመለካት የሚያስችሉ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ተሰጥተዋል፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ምንባቡን

መሰረት በማድረግ የመጻፍ ክሂል ችሎታቸውን ለመለካት የሚያገለግሉ የግለፅ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት በመረዳት፤ የምንባቡን ሀሳብ በራስ አገላለጽ ለመግለጽ የሚያስችሉ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ፣ በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ ሦስተኛው ክፍል ደግሞ የተዘበራረቁ አረፍተ ነገሮችን በትክክለኛው ቅደም ተከተል አስተካክሎ መፃፍ ነው፡፡ ሁለቱ ፈተናዎች የክፍል ደረጃውን፣ የተማሪዎቹን እድሜ እና ችሎታ በአገናዘበ መልኩ በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት አግባብ የተዘጋጁ ናቸው፡፡የተዘጋጀዉ ፈተና የጥናት ቡድኖቹ ከመፈተናቸዉ በፊት በጥናቱ ያልተካተቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተፈትነዉ የፈተናዉ አስተማማኝነት ተረጋግጦ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡

እርማቱን ያካሄዱት በአሰንዳቦ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ሦስት መምህራን ናቸው፡፡ ይህም እርማት በሌሎች መምህራን እንዲፈተሽ ተደርጓል፡፡ ከእርማቱ በፊት ግን አጥኚዋ መረጃው በትክክል ስለመሞላቱ ተመልክታለች፡፡ የሦስቱን መምህራን እርማት ውጤት አማካኝ በመውሰድ የውጤት ትንተናው ተሰርቷል፡፡

### 3.5.2 የፅሑፍ መጠይቅ

የፅሑፍ መጠይቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠው የተማሪዎችን በተመረጠው ዘዴ ምን ያህል እንደሚማሩ ለመለየት የሚያገለግል ነው፡፡ በተማሪዎች የተሞላው የጥያቄ ብዛት12ነው፡፡ ከነዚህ ጥያቄዎች መካከል ሁለቱ ጥያቄዎች ብቻ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ዕድል የሚሰጥ ክፍት ጥያቄ ሲሆን ቀሪዎች ግን አማራጭ መልሶች ያሏቸው ዝግ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ አማራጭ መልስ ያላቸው 10 ያህል ዝግ ጥያቄዎች የሚዘጋጁት የሬቲንግ ስኬል(Rating scale) ወይም ሊከርት ስኬልን (Likert scale) መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የሚኖራቸውን አመለካከት፣ ባህሪና እምነት ሊወክል ይችላል የሚሉትን ከሚሰጣቸው አማራጮች መካከል አንዱን እንዲመርጡ እንዲያስችል ተደርጎ ነው ያለው (2001)፡፡

በዚህ መልክ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ በጥናቱ ተገቢ መሆኑን ለማረጋገጥ በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ እንዲሻሻሉ አስተያየት የተሰጠባቸው ጥያቄዎች ማስተካከያ ከተደረገባቸው በኋላ በ2015 ዓ.ም በአሰንዳቦ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትለሙከራ ቡድን ተመርጠዉ በመማር ላይ ባሉ 32 ተማሪዎች መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

## 3.6 የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ፣ የተነሱ ጥያቄዎችን ለመመለስና የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ከተጠኝ አካላት የተሰበሰቡት መረጃዎች እንደየባህሪያቸው በአግባቡ ከተደራጁ በኋላ አማካይ ውጤትን፣ መደበኛ ልይይትንና ቲ-ቴስትን መሰረት በማድረግ ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ሁኔታ ተተንትነዋል፡፡ ይህን አስመልክቶ Domyel (2007)፣ Brown (2001)ን ዋቢ በማድረግ ሲገልጽ፤ መረጃ መሰብሰብ የአንድ የጥናት ስራ ግማሽ አካል እንደሆነ ብንወስድ ቀሪው ግማሽ ስራ መረጃውን መተንተን ነው በማለት ያስረዳል፡፡ ከዚህም መረጃ መተንተን የጥናቱ መሰረታዊ አካልና ወደ ውጤት የሚያመራን እንደሆነ እንረዳለን፡፡

በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች፣ በአግባቡ ተደራጅተው፣ የማጣራት ስራ ከተከናወነ በኋላ የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል በቅንጫቢዎች በመጠቀም መቅረቡ የመጻፍክሂል ችሎታቸው ላይ የሚያሳየውን መሻሻል በቅድመ ትምህርትና በድህረ ትምህርት ፈተና የተገኙ ውጤቶችን ለማነፃፀር ዳግም ልኬታ ቲ-ቴስት (Repeated Measures t-test) ቀመር አማካይነት ተሰልቷል፡፡ መረጃዎቹም በገላጭና በድምዳሜያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል፡፡

## 3.7 የጥናቱ ሂደት

ከተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤቱ አስተዳደርና ለጥናቱ አስተዋጽኦ ለሚያደርጉ አካላት የምርምሩን ዓላማ በማስረዳት ይሁንታ መልስ በማግኘት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህ መሰረት የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጥኚዋ የክፍል ደረጃውን መማሪያ መፅሀፍ መሰረት በማድረግ የሚዘጋጀውን የትምህርት ይዘት ከመማራቸው በፊት ቅድመ-ትምህርት ፈተና ተፈትነዋል፤ ቅድመ-ትምህርት ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ የተመረጡ ይዘቶችን በተዘጋጁ ቅንጫቢዎች እና ያለ ቅንጫቢዎች አማካይነት ለክፍል ደረጃው በሚቀርበው መማሪያ መጽሐፍ ላይ በመመስረት የሚቀርበውን ትምህርት እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

የትምህርቱ አሰጣጥም ቅድመ ትምህርት ፈተናው እንደተጠናቀቀ፣ በትምህርት ቤቱ ካሉ አራት የቋንቋ መምህራን ተጠኝዎቹን እንዲያስተምር በተመረጠው መምህር፣ የተዘጋጀው ማስተማሪያ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በተዘጋጀው የመማር ማስተማር እቅድ መሰረት ለአራት ሳምንታት፣ በሳምንት ለሁለት ቀን በቀን ለ40 ደቂቃ በተቃራኒ ፈረቃ ትምህርቱ ተካሂዷል፡፡ ትምህርቱ ያካተታቸው ይዘቶችም ጽህፈት፣ ልቦለድ፣ ገፀባህሪያት፣ ዘይቤያዊ አገላለጽ እና አንቀጽ ናቸው፡፡ ተጠኚዎቹም የቀረቡትን የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች መሰረት በማድረግ የተዘጋጁትን የልምምድ ጥያቄዎችን ከተማሩት ትምህርት ጋር እያገናዘቡ እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

## 3.8 የማስተማሪያ አህዶች ዝግጅትና ትግበራ

### 3.8.1 የማስተማሪያ አህዶች ዝግጅት

ቋንቋን ለማስተማር ጥቅም ላይ የሚውሉ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ሲመረጡ፣ ከግንዛቤ የሚገቡ መስፈርቶች ወይም ነጥቦችአሉ፡፡ በእርግጥ የቋንቋ መምህራን ለሚያስተምሩት ቋንቋ የስነጽሁፍ ስራዎች መርጦ ለመገልገል የስነጽሁፍ ስራዎች እጥረት ያጋጥማቸው ይሆናል፡፡ እጥረት ባይኖር እንኳን ከተዘጋጀው የማስተማሪያ መጽሐፍ ውጭእንዳሄዱ የሚደረግ ይሆናል፡፡ ሆኖም ለቋንቋ ማስተማሪያነት በአጋዥነት የሚያገለግሉ የስነጽሁፍ ስራዎች በመምረጥ ለመገልገል ሁኔታው በፈቀደ ጊዜ፤ የስነጽሁፍ ስራዎቹን ለቋንቋው ማስተማሪያነት ከመገልገል በፊት በጥንቃቄ መምረጥና መገምገም እንደሚያስፈልግ የመስኩ ባለሙያዎች ይገልፃሉ፡፡

በክፍል ውስጥ ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጡ ስነጽሁፋዊ አህዶች ሊያሟሏቸው ስለሚገቧቸው መስፈርቶች በርካታ የዘርፉ አጥኚዎች ብዙ ብለዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Lazar (1993)፣ Hill (1986)፣ Carter and Long (1991)፣ Mckay (1986) እና Brumfit and Carter (1986) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከአህድ መምረጫ መስፈርቶች ውስጥም የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ፣ የስነጽሁፋዊ ዳራዊ ዕውቀትና ከስነጽሁፋዊ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦችን ባገናዘበ መልኩ መምረጥ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ የአህድ መምረጫ መስፈርቶችም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

#### 3.8.1.1 የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ባገናዘበ መልኩ መምረጥ

እንደ Hill (1986) ገለፃ ተማሪዎች አንድን የስነጽሁፍ ስራ የመረዳትና የማገናዘብ ችሎታቸው እንደየመጡበት አካባቢና እንደያደጉበት ማህበረሰብ ቋንቋ አጠቃቀም ሊለያይ ይችላል፡፡ ለማስተማሪያነት የቀረበውን ስነጽሁፋዊ አህድ አንብበው የመረዳት አቅም /ችሎታ/፣ የቀረበውን አህድ በቶሎ የመለማመድ ሁኔታ ለነዚህ ዳራዎች ባላቸው ቅርበት ሊፋጠን ወይም ሊጓተት ይችላል፡፡ ከተማሪዎቹ ባህል ውጭ በሆነ ሌላ ባህል ላይ የተመሰረተ የስነጽሁፍ ስራን ለመገንዘብ ተማሪዎቹ ስራው ስለተመሰረተበት ባህል ዳራዊ ዕውቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም ለቋንቋ ማስተማሪያ የስነጽሁፍ ስራዎች ሲመረጡ "በውስጣቸው የተንፀባረቀው ባህላዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ እንዲሁም ለተማሪዎቹ ገለፃውን ለመረዳት የሚያግዛቸው ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እውቀታቸው እስከምን ድረስ ነው?" የሚለውን ጥያቄ ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ግን ሁልጊዜ ለቋንቋ ማስተማሪያነት

የሚያገለግሉ ስነጽሁፋዊ ስራዎች ተማሪዎቹ በሚያውቋቸው ጉዳዮች፣ በዘመናቸውና በአካባቢያቸው ላይ ብቻ ያተኮሩ መሆን አለባቸው ወደሚል መደምደሚያ አያደርስም፡፡

Hill (1986) አክለው እንደገለፁት ተማሪዎቹ ካለፉበትና ከሚገኙበት እውነተኛ የህይወት ገጠመኝ ለየት ያሉ ማህበራዊና ባህላዊ የህይወት ገጠመኞችን የሚያንፀባርቅ የስነጽሁፍ ስራ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውል አዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኖች አሉት፡፡ ከአሉታዊ ጎኖች ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

- በስነጽሁፍ ውስጥ የተንፀባረው ማህበራዊ ልማድ ከተማሪዎቹ በመለየቱ የተነሳ ግራ መጋባት ይፈጠራል፡፡

- በስነጽሁፍ ስራው ውስጥ የቀረበው ማህበራዊ አመለካከትና አተያይ ከተማሪዎቹ የተለየ በመሆኑ ለስራው ባዳነት ሊንፀባረቅ ይችላል፡፡

- ከማህበራዊ ቦታዎች ረገድ በስነጽሁፍ ስራው ውስጥ የተንፀባረው ተማሪዎቹ ከሚያውቁት የተለየ ይሆን ይሆናል፡፡

- በሀይማኖታዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ረገድ በስነጽሁፍ ስራው ውስጥ የቀረበው ከተማሪዎቹ እውነተኛ ገጠመኝ ሊለይ ይችላል፡፡

ቋንቋውን የሚማሩት ተማሪዎች ካለፉበትና ከሚገኙበት እውነተኛ የህይወት ገጠመኝ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ማህበረ ባህላዊ ጉዳዮችን የሚያንፀባርቅ የስነጽሁፍ ስራን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመገልገል ረገድ ከሚጠቀሱና አወንታዊ ጎኖች ናቸው ከሚባሉት ውስጥ ደግሞ የሚከተሉት ይገኛሉ፡፡

- የተማሪዎችን የህይወት ልምድ አድማስ ያሰፋል፡፡
- ተማሪዎቹ ስለአለም ያላቸውን አመለካከት ያጎለብታሉ፡፡
- ለተማሪዎቹ አዳዲስ የህይወት ገጠመኞችን ያስገኛል፡፡

ስለዚህ ለቋንቋ ትምህርት የሚውለው አሀድ የተማሪዎችን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ባህላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ሊመጣ የሚችል ልዩነትን የሚያስወግድ ቡሆን ይመረጣል (Hill 1986)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት ማብራሪያዎች ስነጽሁፋዊ አሀዶች ለማስተማሪያነት ሲመረጡ የተማሪውን ባህላዊ ዳራ ከግምት ማስገባት አስፈላጊ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ አጥኚዋም ይህንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለማስተማሪያነት የተዘጋጁትን አሀዶች ለመምረጥ ጥረት አድርጋለች፡፡

### 3.8.1.2 የተማሪዎችን የስነጽሁፍ ዳራዊ ዕውቀት ባገናዘበ መንገድ መምረጥ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊውል የታሰበው የስነጽሁፍ ስራ ከተማሪዎች የቋንቋ ክሂል ጋር (the students Linguistic Proficiency) ጋር የሚጣጣም መሆን እንዳለበት Hill (1986) ያስገነዝባሉ፡፡ ይኸውም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውሉ የስነጽሁፍ ስራዎች ሲመረጡ በቋንቋ አጠቃቀምና ብስለት ደረጃው (Linguistic and stylistic Level) ቋንቋውን ከሚማሩት ተማሪዎች ችሎታ ጋር ምን ያህል እንደሚጣጣሙ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የስነጽሁፍ ስራዎቹ በቃላት አጠቃቀማቸውና በአረፍተ ነገር አወቃቀራቸው ረገድ ከተማሪዎቹ ችሎታ በላይ ወይም በታች እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያሻል፡፡ በስነጽሁፍ ስራዎቹ ውስጥ የሚገኙት አዳዲስ ቃላት ትርጉማቸው አውድን መሰረት በማድረግ የሚደረስባቸው ቢሆኑ ይመረጣል፡፡ ምክንያቱም የስነጽሁፍ ቋንቋ ከተለመደው የቋንቋ አጠቃቀም (ከህዝቡና ከተለመደው) ወጣ ያለ ይሆናል፤ የስነጽሁፋዊ ቋንቋ አገላለፅ በአብዛኛው ከቋንቋው የተለመደ ህግ ያፈነገጠ መሆን የተለመደ ነው (Hill 1986)፡፡ እንዲሁም Hill (1986) በተመሳሳይ በሰጡት ገለፃ የስነጽሁፍ ስራዎች በዘይቤዎች፣ በዘዬዎች የተሞላ፣ በአረፍተ ነገር ደረጃም ቢሆን ከተለመደው የቋንቋው የአረፍተ ነገር አወቃቀር ውጭ የሚሆንበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጠው የስነጽሁፍ ስራ በቋንቋው ከፍተኛ ችሎታ አላቸው ለሚባሉት ተማሪዎች ሳይቀር ሊያስቸግራቸው ይችላል፡፡ ይህን ለማስወገድም የስነጽሁፍ ስራው ተመርጦ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ከመዋሉ በፊት በጉዳዩ ዙሪያ ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎችን እያነሱ መመርመር ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ ከሚነሱ ጥያቄዎች ውስጥም የሚከተሉት ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

- ተማሪዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊመረጥ በታሰበው የስነጽሁፍ ስራ ውስጥ ከሚገኙት ከተለመደው ወጣ ያሉ አገላለፆችና አገባቦች ጋር የመተዋወቅ ደረጃቸው እስከምን ድረስ ነው?
- ተማሪዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሊመረጥ በታሰበው የስነጽሁፍ ስራ ውስጥ ካለው ቋንቋ ውስጥ ምን ያህሉን ይገነዘቡታል? ምን ያህሉንስ አይገነዘቡትም?

- ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጥ በታሰበው የስነጽሁፍ ስራ ውስጥ ያለው ከተለመደው ወጣ ያለ የቋንቋ አጠቃቀም ተማሪዎቹ ቋንቋውን እንዲማሩ ያበረታታል ወይስ እንቅፋት ይሆናል? ተስፋ ይሰጣል ወይስ ተስፋ ያስቆርጣል? ፍላጎትን ያነሳሳል ወይስ ይቀንሳል?
- ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጥ በታሰበው የስነጽሁፍ ስራ ተማሪዎች እንዲማሩና እንዲያውቁ ከሚፈለገው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ይጣጣማል ወይስ ይቃረናል?

Carter and Long, (1991) በበኩላቸው ስነጽሁፋዊ አሀዶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ለመጠቀም ሲመረጡ፣ ስነጽሁፋዊ አሀዶቹ ሁሉም ተማሪዎች ሊያገኟቸው የሚችሉ፣ ከቋንቋ ተናጋሪናከዘመኑ ጋር ወካይነት ያላቸው፣ ያልተሰለቹና ለንባብ ሰፊ ጊዜን የማይጠይቁ ስራዎች የበለጠ ተመራጭነት ይኖራቸዋል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ መስፈርቶች ከፍ ሲል አሀድ በሚመረጥበትጊዜ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ በአሀዱ ውስጥ ስነልሳናዊና ጽንሰሃሳባዊ ችግር እንዳይኖረው ከመመርመሩ ላይ ነው፡፡

## 3.8.1.3 ከስነጽሁፍ ስራው ጋር የተያያዙ ሌሎች ነጥቦች

የስነጽሁፋዊ ስራዎችን በመምረጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ለማዋል ሲታሰብ፣ ከግንዛቤ መግባት አለባቸው ከሚባሉት ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች ውስጥ የስነጽሁፍ ስራው በስፋት የመገኘት ሁኔታ፣ የስነፅሁፍ ስራው የተተንታኝነት ደረጃ እና በትምህርትነት ከሚሰጠው ቋንቋ መርህ ትምህርት ጋር ያለው የዝምድና ደረጃ የሚሉት የሚጠቀሱ ናቸው (Lazar 1993)፡፡

በአጠቃላይ ዘመንፈስ (1991)፣ Williams (1986)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ለቋንቋ ትምህርት የሚያገለግሉ አሀዶች በሚመረጡበት ጊዜ ቅድሚያ መስጠት ያለበት አሀዶቹ ለቋንቋ ትምህርት በሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ላይ እንጅ በምንባቦቹ ይዘት ባይሆን ይመረጣል፡፡ በየክፍል ደረጃው የሚቀርቡት አሀዶች ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎች የየአሀዶቹን ይዘት ተረድተው በተግባር እንዲተረጉሙ ሳይሆን፣ በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የታቀዱትን ዓላማዎች እውን ለማድረግ የሚያግዙ መሆን አለባቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የሰፈረው ዓላማ ተማሪዎች በቋንቋው ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መፃፍ እንዲችሉ ከሆነ የአሀዶቹ አመራረጥና አደረጃጀትም እነዚህን ዓላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ቢሆኑ ተመራጭ ነው፡፡

እነ Borja j. ojeda and Marina Torralbo አንድን ስነጽሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስንመርጥ የተለያዩ መስፈርቶችን መከተል ያለብን መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ እነሱም፡-

1. የተማሪዎች ባህላዊ ዳራ፡- የተመረጠው ስነጽሁፍ ከተማሪዎች ባህላዊ፣ ማህበራዊ እናፖለቲካዊ ዳራ የራቀ ወይም የቀረበ መሆኑ ፅሁፉን በቀላሉ እንዲረዱት ወይም ለመረዳት እንዲዘገዩ ብሎም እንዲጠሉት ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ የሚመረጠው ፅሁፍ ከተማሪዎች ባህላዊ ዳራ ጋር የተመጣጠነ ቅርርቦሽ ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
2. የተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ብቃት ፡- ጽሁፉ የቀረበበት የስነ-ልሳን ብቃት ለመገምገም ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡
   - ተማሪዎች በፅሁፉ ውስጥ ያለው ሀሳብ ተገልብጦ ቢፃፍ ወይም ተዛብቶ ቢቀርብ ሊገነዘቡ ወይም ሊረዱ የሚችሉበት ከቋንቋ የአጠቃቀም ልማድ ጋር ቅርበት አላቸው?
   - ተማሪዎች ምን ያህሉንበፅሁፍ ውስጥ ያለውን ቋንቋ መረዳት ይችላሉ?
   - ተማሪዎች ፅሁፉን ማጥናታቸውን አስደሳችና ጠቃሚ አድርገው ይቀበሉታል ወይስ በቋንቋው ክብደት ምክንያት የስሜት መቀዝቀዝ ይታይባቸዋል?
   - ምንም እንኳን ቋንቋው ከባድና አስቸጋሪ ቢሆንም ተማሪዎች በሌላ ምክንያት ተገፋፍተው ፅሁፉን ሊያነቡት ይችላሉ?
3. የተማሪዎች ስነ-ጽሁፋዊ ዳራ፡- ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጥሩ የሆነ የስነ-ጽሁፍ ብቃት ካላቸው በሁለተኛ ቋንቋቸው የሚቀርበውን ስነ-ጽሁፍ በተመሳሳይ ሁኔታ መተንተን ወይም ማብራራት ይችላሉ፡፡
4. የፅሁፉ መገኘት ፡- የታተሙ ወይም ያልታተሙ ጽሁፎች በቀላሉ ሊገኙ የሚችሉበት መሆን ይኖርበታል፡፡
5. የፅሁፉ እርዝማኔ፡- የሚመረጠው ጽሁፍ በጣም አጭር ወይም ረጅም መሆን የለበትም፡፡

ከቀረቡት ገለፃዎች የስነ-ጽሁፍ አሀዶችን ለማስተማሪያነት ለመጠቀም እንዴት መመረጥ እንዳለባቸውና የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎችን መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ቋንቋውን ከሚማሩት ተማሪዎች ረገድ ከግንዛቤ ከሚገቡ ነጥቦች ውስጥም የሚከተሉት በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

- የተማሪዎች ማህበራዊ ሁኔታ
- የተማሪዎች የቋንቋ ዳራ
- የተማሪዎች ስነ-ጽሁፋዊ ዳራ
- የተማሪዎች እድሜ

- የተማሪዎች የእውቀት ደረጃ
- የተማሪዎች ፍላጎት የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በአጠቃላይ አንድ የስነ-ጽሁፍ አሀድ በማስተማሪያነት ሲመረጥ ከሞላ ጎደል ከላይ የቀረቡትን አስረጂዎች መሰረት ማድረግ እንዳለበት የመስኩ ባለሙያዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይሁንና ለዚህ ጥናትም ለማስተማሪያነት የተዘጋጁት አሀዶች ከላይ የቀረቡትን ገለፃዎች መሰረት በማድረግ ለመምረጥ ተሞክሯል፡፡

### 3.8.1.4 የማስተማሪያ አሀዶች ትግበራ

Collie and Slater (1987) እንደገለፁት የስነ-ጽሁፍ አሀድ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲውል ሶስት የአቀራረብ የሂደት ደረጃዎችን ሊከተል ይገባል፡፡ የመጀመሪያው ከስራው ጋር መተዋወቅ ነው፡፡ ሁለተኛው ደረጃ የስነ-ጽሁፍ አሀዱን በማንበብ የመረዳትና በጥልቀት የማወቅ ሲሆን፣ ሶስተኛው አሀዱን የመተንተንና ትርጓሜ የመስጠት ተግባራት የሚከናወንበት ነው፡፡

የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ለማስተማሪያነት በተመረጠው ስነ-ጽሁፋዊ አሀድ አማካይነት ተማሪዎቹ ከገፀባህሪያት አንጻር፣ ከዘይቤያዊ አገላለጽ አንፃር፣ ከቃላት አጠቃቀም አንፃር፣ ከአረፍተ ነገር ቅንብር አንፃር ወዘተ ገምግመው እንዲጽፉ ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ስነጽሁፋዊ አሀዱን መሰረት በማድረግ የቀረቡትን ጥያቄዎች ተንትነውና አብራርተው እንዲጽፉ በማድረግ፣ ሀሳብ እንዲለዋወጡና ምጋቤ ምላሽ እንዲያገኙ ጥረትተደርጓል፡፡ ትምህርቱ የተሰጠው በሌላ የአማርኛ ቋንቋ መምህር ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች መደበኛ ትምህርታቸውን በማይነካ መልኩ (በተቃራኒ ፈረቃቸው) ለ4 ሳምንታት በሳምንት ለሁለት ቀን በቀን ለ40 ደቂቃ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### 4.1 የውጤት ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማበአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች መፃፍን በማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለው ሚና መመርመር ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት በፈተና እናበጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡን መረጃዎች በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች መጻፍን ማስተማርየተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል ፍላጎት ለማሻሻል ይረዳ ይሆን? ጽህፈትን በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በተማሩ ተማሪዎች እና ያለአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ወይም በተለመደው የተማሩ ተማሪዎች መካከል የመጻፍ ችሎታ ልዩነት ይኖረዋል ወይስ ልዩነት አይኖረውም ይሆን?የሚሉ መሰረታዊ የምርምሩጥያቄዎች በቅደም ተከተል ተተንትነዋል፡፡

### 4.2 ከፈተናዎቹ የተገኘ የጥናቱ ውጤት ትንተና

በፈተናው የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደየ ባህሪያቸው ተደራጅተው በቅደም ተከተላቸው መሠረት እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡ የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ንፅፅር ሠንጠረዥ 4.1ን እና 4.2ን ይመልከቱ፡፡

የሙከራ ቡድኑ ተጠኝዎች ከልምምዱ በፊት ያላቸውን የመፃፍ ችሎታ መለየት አስፈላጊ በመሆኑ በተሰጣቸው ፈተና የቁጥጥር ቡድኑን እና የሙከራ ቡድኑን ቅድመ ትምህርት የመፃፍ ችሎታ ከ50% ያስመዘገቡትን ውጤት ንፅፅር ሠንጠረዥ 4.3ን ይመልከቱ፡፡ እንዲሁም የሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ንፅፅር ሠንጠረዥ 4.4ን ይመልከቱ፡፡ በዚህ መሰረት የሙከራ ቡድኑ ቅድመ እና ድህረ ፈተና እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ እና ድህረ ፈተና ውጤት ንፅፅር በሠንጠረዥ 4.5 ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ መፃፍን ማስተማርየተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ፍላጎት ለማሻሻል ይረዳ ይሆን የሚለው ጥያቄ ለመመለስ በቅድመ ትምህርት እና በድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበውን መረጃ በመጀመሪያ በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና በድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትነዋል፡፡ በሁለቱ ፈተናዎች አማካይ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩንና አለመኖሩን ለመፈተሽም ዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተግባር ላይ ውሏል፡፡

በሁሉም ረገድ የተሰራው ስሌት ውጤት በሠንጠረዥ 4.1 እና 4.2 ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.1 የሙከራቡድን የቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት)

| ውጤት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | t-cri | የP-ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 32 | 23.88 | 8.783 | 7.033 | 31 | 2.042 | 0.000 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | | 31.38 | 8.492 | | | | |

በሠንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በቀረበው ትምህርት የተማሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች በዚህ አቀራረብ ሳይማሩ ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት መካከል ልዩነት መኖሩን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ተማሪዎቹ በቅድመ ትምህርቱ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (23.88) ሲሆን በድህረ ትምህርት ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት (31.38) አንሶ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን መማራቸው በውጤታቸው ላይ ለውጥ እንዳስከተለ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የድህረ ትምህርት መደበኛ ልይይት (8.492) ከቅድመ ትምህርት መደበኛ ልይይት (8.783) ያነሰ መሆኑን ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ሆኖም የአማካዮቹን ልዩነት እንዲሁ በማየት ልዩነት አለ ወይም የለም በሚል ብቻ መተማመን አይቻልም፡፡ ልዩነቱ አስተማማኝ መሆን አለመሆኑን በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት በቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡

በድህረ ትምህርት እና በቅድመ ትምህርት አማካዮች መካከል ያለው ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ ይህም (የቲ-ዋጋ 7.003፤ የነፃነት ደረጃ = 31 የP-ዋጋ 0.000 በመሆኑ $p<0.05$) ሆኗል፡፡ በሁለቱ አማካዮች መካከል ልዩነት የመጣው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን በማስተማር መሆኑን ሊጠቁምይችላል፡፡ የስታትስቲክስ ውጤቱ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ በጎ ተፅእኖ እንዳለው ያመለከተ ይመስላል፡፡

ሠንጠረዥ 4.2 የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት)

| ውጤት | የናሙና ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | t-cri | የP-ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና | 32 | 23.69 | 8.411 | 1.531 | 31 | 2.042 | .136 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና | | 24.81 | 7.377 | | | | |

$p>0.05$

በሠንጠረዥ 4.2 እንደ ተመለከተው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ባልተማሩ የጥናቱ ተሳታፊዎች አማካይ ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ተማሪዎቹ በቅድመ ትምህርቱ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (23.69) ሲሆን በድህረ ትምህርት ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (24.81) ብዙም ልዩነት ሳይታይ ተቀራራቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም የጥናቱ ተሳታፊዎች በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን አለመማራቸው በውጤታቸው ላይ ለውጥ እንዳላሳየ ጥናቱ አመልክቷል፡፡ መደበኛ ልይይትንም በተመለከተ የድህረ ትምህርት መደበኛ ልይይት (7.377) ከቅድመ ትምህርት መደበኛ ልይይት (8.411) ብዙም ያላነሰ መሆኑን ውጤቱ ያመለክታል፡፡ ሆኖም የአማካዮቹን ልዩነት እንዲሁ በማየት ልዩነት አለ ወይም የለም በሚል ብቻ መተማመን አይቻልም፡፡ ልዩነቱ አስተማማኝ መሆን አለመሆኑን በስታትስቲክስ መረጋገጥ ስላለበት በቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በድህረ ትምህርትና በቅድመ ትምህርት አማካዮች መካከል ያለው ልዩነቱ ጉልህ መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ ይኸውም (ቲ=1.531፤ የነፃነት ደረጃ =31 ፤ $p>0.05$) ይህም በሁለቱ ውጤት መካከል ያለው ልዩነት በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሁለቱ አማካዮች መካከል ሰፊ ልዩነት ያልመጣው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ባለመማር ወይም በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን መማራቸው መሆኑን ሊጠቁም ይችላል፡፡ የስታቲስቲክስ ውጤቱ በተለመደው አቀራረብ (ያለ አጭር ልቦለድ ቅንጫቢ) ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለው አስተዋፅኦ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ያመላከተ ይመስላል፡፡

በጥናቱ ሊመለስ የተፈለገው ሁለተኛው ጥያቄ ቋንቋን በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ማስተማር በተማሪዎች የመፃፍ ፍላጎት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖረው ይሆን? የሚል ነበር፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቅድመ ትምህርትና

ድህረ ትምህርት ፈተና የተሰበሰበው መረጃ አማካይ ውጤት ፣ መደበኛ ልይይትና በድምዳሜያዊ ስታቲስቲክስ ተተንትኗል። ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.3 እና 4.4 ተመልክቷል።

ሠንጠረዥ 4.3 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ተለዋዋጭ | | | | | | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | t-cri | የP-ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | | | | | |
| ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 32 | 23.88 | 8.783 | 32 | 23.69 | 8.411 | 0.087 | 62 | 2.042 | 0.931 |

p>0.05

ከሠንጠረዥ 4.3 መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 23.88 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ደግሞ 23.69 ነው። የሁለቱም ቡድኖች በቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ተመሳሳይነት ያላቸው ይመስላሉ። እንዲሁም የሙከራ ቡድን የመደበኛ ልይይት 8.783 ሲሆን፣ የቁጥጥር ቡድኑ የመደበኛ ልይይት ደግሞ 8.441 ነው። ይህም የሁለቱም ቡድኖች የመደበኛ ልይይት ውጤት ተቀራራቢነት እንዳላቸው ያሳያል። ከዚህም በሁለቱ ቡድኖች የተመዘገቡት የፈተና ውጤቶች ካማካያቸው ተቀራራቢ ርቀት ስርጭት እንዳላቸው ያሳያል። ነገር ግን የአማካይ ውጤትን ብቻ በማየት በመካከላቸው ልዩነት አለ ወይም የለም ለማለት ያዳግታል፤ ስለዚህ ውጤቱ በስታቲስቲክስ መረጋገጥ አለበት። ይህም በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ የ"t" ስሌት ዋጋ (ቲ-ቴስት) 0.087 ሲገኝ፣ የP ስሌት ዋጋ 0.931 ሲሆን በ0.05 የጉልህነት ደረጃ /significance level/፣ በ62 የነፃነትደረጃ /Degree of freedom/ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ"t" ሠንጠረዥ ዋጋ (t-cri) 2.042 ሆኗል። በዚህም መሰረት የ"t" ዋጋ (ቲ-ቴስት) 0.087 ከሠንጠረዥ ዋጋ (t-cri) 2.042 አንሶ ተገኝቷል።እናም በሁለቱ መካከል ልዩነት እንደሌለ ውጤቱ ያመላከተ ይመስላል።

ሌላው በፈተናአማካይነት የተሰበሰበው መረጃ የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት ነው። የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛው መንገድ፣ የሙከራ ቡድኑን ደግሞ አጥኚዋ ባዘጋጀችው የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ከተማሩ በኂላ ሁለቱም ቡድኖች አንድ ዓይነት ፈተና ተፈትነው ያስመዘገቡት

ውጤት (የቁጥጥር ቡድንና የነከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት) በሠንጠረዥ 4.4 ተነፃፅሮ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 4.4 የሙከራ ቡድንና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ንፅፅር (በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት)

| ተለዋዋጭ | | | | | | የቲ-ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | t-cri | የP-ዋጋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ ቡድን | | | የቁጥጥር ቡድን | | | | | | |
| ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | ናሙና | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | |
| 32 | 31.38 | 8.492 | 32 | 24.81 | 7.377 | 3.300 | 62 | 2.042 | 0.002 |

$p<0.05$

ሠንጠረዥ 4.4 እንደሚያሳየው በሙከራ ቡድን እና በቁጥጥር ቡድኑ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ መማርና አለመማር ምክንያት የፈተና ውጤት ላይ የታየው ልዩነት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች አማካይ ውጤት (31.38) ከቁጥጥር ቡድን አማካይ ውጤት (24.81) ብልጫ አሳይቷል፡፡ የቁጥጥር ቡድን መደበኛ ልይይት (7.377) ከሙከራ ቡድን መደበኛ ልይይት (8.492) አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይሁንና አማካይ ውጤትን እንዲሁ በማየት ብቻ ልዩነት እንዳለውና እንደሌለው ማረጋገጥ ስለማይቻል በቲ-ቴስት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በስታቲስቲክስ ስሌቱ የP ስሌት ዋጋ 0.002 ሲሆን፤ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ62 የነፃነት ደረጃ (ቲ= 3.300 df= 62፣ P<0.05) መሆኑን ውጤቱ አሳይቷል፡፡ ይኸም በሙከራ ቡድንና በቁጥጥር ቡድን የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ሰፊ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡ ይህ የሚጠቁመው የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በመማራቸው፣ ከቁጥጥር ቡድኑ በላይ የመፃፍ ችሎታቸው መሻሻሉን ነው፡፡ ይህንን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የሁለቱን ቡድኖች ቅድመ ፈተናና ድህረ ፈተና በማነፃፀር በሠንጠረዥ 4.5 መመልከት ይቻላል፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 የየቡድኖቹ የቅድመና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ተናጠላዊ ንፅፅር (በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት")

| ተጠኝ ቡድን | የፈተና አይነት | የፈተና ውጤት | | | ተቀንሶ የተገኘ የአማካይ ውጤት ልዩነት | ተቀንሶ የተገኘ የመደበኛ ልይይት ልዩነት | የነፃነት ደረጃ (df) | የt-cri (table value) | የተሰላ የ"t"ዋጋ (t-test) | የፐ-ዋጋ | ጉልህነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | | | | | | | |
| የቁጥጥር ቡድን | ቅድመ ትምህርት | 32 | 23.69 | 8.411 | 1.12 | 1.034 | 31 | 2.042 | 1.531 | .136 | የለም |
| | ድህረ ትምህርት | | 24.81 | 7.377 | | | | | | | |
| የሙከራ ቡድን | ቅድመ ትምህርት | 32 | 23.88 | 8.783 | 7.5 | 0.291 | 31 | 2.042 | 7.033 | 0.000 | አለ |
| | ድህረ ትምህርት | | 31.38 | 8.492 | | | | | | | |

- የቁጥጥር ቡድን፡- ቅድመ ትምህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት የለውም ስለዚህ /p>0.05/ ሲሆን
- የሙከራ ቡድን፡- ቅድመ ትመህርት ፈተና እና ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት አለው ስለዚህ /p<0.05/ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 4.5 እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 24.81 ከቅድመ ትምህርትፈተና አማካይ ውጤት 23.69 ጋር ሲነፃፀር በልጦ የታየው በ1.12 ብቻ ነው፡፡ ይህ ልዩነት ጉልህነት እንዳለውና እንደሌለው በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት" (repeated measure sample t-test) ተፈትሿል፡፡ በፍተሻውም የ"t" ስሌት ዋጋ (t-test) 1.531 ሲሆን፣ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ31 የነፃነት ደረጃ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ"t" ሠንጠረዥ ዋጋ (t-cri) 2.042 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የ"t" ስሌት ዋጋ 1.531 ከሠንጠረዥ የ"t" ዋጋ 2.042 ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት፣ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት አለማሳየቱን ሊያመለክት ይችላል፡፡

ይህም የቁጥጥር ቡድኑ በተለመደው አቀራረብ መማራቸው የመፃፍ ችሎታቸውን ለማሻሻል የጎላ አስተዋጽኦ እንደሌለው የሚያሳይ ይመስላል፡፡

በሌላ መልኩ ሲታይ የሙከራ ቡድኑ የድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 31.38፣ ከቅድመ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት 23.88 ጋር ሲነፃፀር በ7.5 ልቆ ይታያል፡፡ ልዩነቱ የጎላ መሆኑን ብሎም ብልጫ እንዳለው የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ይህ ልዩነት ጉልህነት እንዳለውና እንደሌለው በዳግም ልኬት ናሙና "ቲ-ቴስት" (repeated measure sample t-test) ተፈትሿል፡፡ በፍተሻውም የ"t" ስሌት ዋጋ (t-test) 7.033 ሲሆን፣ በ0.05 የጉልህነት ደረጃ፣ በ31 የነፃነት ደረጃ፣ ባለሁለት ጫፍ ፍተሻ የ"t" ሠንጠረዥ ዋጋ (t-cri) 2.042 ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የ"t" ስሌት ዋጋ 7.033 ከሠንጠረዥ የ"t" ዋጋ 2.042 ሲነፃፀር አንሶ ተገኝቷል፡፡ ይህም ቡድኑ በድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት፣ ከቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት ማሳየቱን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ይህም የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ መማራቸው የመፃፍ ችሎታቸው እንዲሻሻል የጎላ አስተዋፅኦ እንዳደረገ የሚያሳይ ይመስላል፡፡ ከዚህ የተነሳ በሙከራ ቡድኑ ቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት እና ድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት መካከል የጎላ ልዩነት /p<0.05/ ታይቷል፡፡ በአንፃሩ ግን በቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት እና የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ጉልህ ልዩነት አለመታየቱን /p>0.05/ መሆኑን ትንተናው አመላክቷል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች በመማሩ ቀድሞ ከነበረው የተሻለ ውጤት ማምጣት ችለዋል ማለት ይቻላል፡፡ በሁለቱ አማካዮች መካከል ልዩነት የመጣው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋንበማስተማር እና ባለማስተማር ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር በተለመደው አቀራረብ ከማስተማር በላይ የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ያሻሽላል፡፡ ወደሚል መደምደሚያ መድረስ ይቻላል፡፡ ስለዚህም ከልምምድ በኋላ በቁጥጥር ቡድኑና በሙከራ ቡድኑ መካከል የመፃፍ ችሎታ መሻሻል ልዩነት አይታይም የሚለው የጥናቱ አልቦ መላምት /$H_0$/ተቀባይነት አላገኘም፡፡ ይህ ማለት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ማሻሻል ላይ ልዩነት አይኖርም (የለም) የሚለው መላምት ውድቅ ይሆንና፣ ተለዋጩ መላምት /$H_1$/ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ መሻሻል ላይ ልዩነት አለ የሚለው መላምት ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ሠንጠረዥ 4.6 የጽሁፍ መጠይቅ ውጤት ትንተና

| የጥያቄዎቹ ተ.ቁ | ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ብዛት | |
|---|---|---|
| | አዎ | አይ |
| 1 | 28 | 4 |
| 2 | 28 | 4 |
| 3 | 28 | 4 |
| 4 | 28 | 4 |
| 5 | 28 | 4 |
| 6 | 29 | 3 |
| 7 | 28 | 4 |
| 8 | 29 | 3 |
| 9 | 29 | 3 |
| 10 | 28 | 4 |

ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከላይ በፈተና ከተገኘው ውጤት ጋር ተደጋጋፊነት ያለው ነው፡፡ በዚህም የመጠይቅ ውጤት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው በክፍል ውስጥ የተካሄደውን የትምህርት ትግበራ በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ በማካተት በቀረበው ጥያቄ መሰረት በውጤቱ የተገኙ ምላሾችን ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ በዚህም መሠረት በሙከራ ቡድኑ የቀረቡት አስር ዝግ እና ሁለት ክፍት በአጠቃላይ አስራሁለት ጥያቄዎች ሲሆኑ ጥያቄዎቹን በሦስት ዋና ዋና ክፍል በመመደብ ተተንትነዋል፡፡

ክፍል አንድ፡- ለሙከራ ቡድኑ ትምህርት በሚሠጥበት ጊዜ በመማር ማስተማሩ የነበረውን ሂደት በተመለከተ መመሪያ አንድ ተራቁጥር 2፣ 5፣ 7 እና 12 ለቀረበው መጠይቅ ከሙከራ ቡድን ከነበሩት 32 ተማሪዎች መካከል 28 ተማሪዎች አዎ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 4ቱ ተማሪዎች ደግሞ አይ የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም (Hill 1986) እና (ዘሪሁን 2005) ‹‹ ስነፅሁፍ አዕምሮን የማነቃቃት ሀይል ያለው በመሆኑ የቋንቋን ትምህርት በምናስተምርበት ጊዜ ስነፅሁፋዊ አሀዶችን በመርጃ መሳሪያነት ብንጠቀምባቸው ትምህርቱን ሳቢ እና በንቃት የሚከናወን እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡ በማለት ከገለፁት ሀሣብ እና (Obsen 1995) የስነፅሁፍ ሥራ

ሳቢ በመሆኑ በተማሪዎች መካከል ባለው ውይይት የተሳታፊነት ደረጃውን ከፍ ያደርጋል፡፡ ተማሪዎች ተውኔት፣ ልቦለድ፣ ግጥም ሲያነቡ የማንበብ እና የመፃፍ ክሂላቸውን ያዳብራሉ በማለት በጥናታቸው የገለፁትን ሃሣብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

ክፍል ሁለት፡- በተማሪና በመምህሩ እንዲሁም በተማሪ እና በተማሪ መካከል ያለውን መስተጋብር በተመለከተ በመጠይቁ መመሪያ አንድ ተራቁጥር 6 እና 8 ከሞሉት የሙከራው 32 ተማሪዎች መካከል 29 ተማሪዎች አዎ ያሉ ሲሆን 3 ተማሪዎች ደግሞ አይ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የመፃፍ ክሂል ተከታታይነት ያለው ልምምድ ካልተደረገ፣ ገንቢና ትምህርት ሰጪ የሆነ ምጋቤ ምላሽ ካልተሰጠ፣ የመምህራን ክትትልና ድጋፍ ካልተደረገበት በሚፈለገው መልኩ ሊጎለብት አይችልም በማለት የገለፁት (የWilliams 2003) እና (የZamel 1982) ሃሣብን የሚደግፍ ይመስላል፡፡

ክፍል ሦስት፡- የተማሪዎችን የተሳትፎ ሁኔታ ለመገምገም በመጠይቅ መመሪያ አንድ ጥያቄ ቁጥር 1፣ 3፣ 4፣ 9፣ 10 እና 11ከሞሉ የሙከራ ቡድኑ 32 ተማሪዎች የሚከተለው ምላሽ ተገኝቷል፡፡ ይኸውም 28 ተማሪዎች አዎ የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 4 ተማሪዎች ደግሞ አይ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህም የሚያመለክተው የሙከራ ቡድኑ ትምህርቱን በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በመማራቸው ለመፃፍ እንዳነሣሣቸው እና ፍላጎት ማጣትን እንዳስወገደላቸው ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም በማስተማሪያ ቅንጫቢዎቹ ውስጥ ያሉትን መልመጃዎች በመስራታቸውና ሠፊ ጊዜን ወስደው ተከታታይ ልምምድን በማድረጋቸው የመፃፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉ ረድቷቸዋል ወደ ሚል እሳቤ ያደርሳል፡፡ ይህም (Hill 1986) ስነፅሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማካተት ለተማሪዎች ጠቅላላ እውቀት፣ አዕምሮአዊ ብስለት፣ ማህበራዊና ሥነምግባራዊ እድገት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር እውነተኛ አውድን ስለሚፈጥርና ተማሪዎችን ስለሚያሳትፍ የቋንቋውን ትምህርት የተሳካ ያደርገዋል በማለት ከሠጡት ሀሳብ ጋር ይደጋገፋል፡፡

## 4.3 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመፃፍ ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በመሆኑም በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ

ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና፤ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎች የመፃፍ ችሎታ ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት ይኖረው አይኖረው እንደሆነ ለመፈተሽ መረጃዎች በገላጭና በድምዳሚያዊ ስታቲስቲክሶች ተተንትነዋል። በውጤት ትንተናው በቅድሚያ ምላሽ የተሰጠው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል ረገድ ያለውን ሚና የሚመለከት ነው። በሠንጠረዥ 4.1 (ገጽ፣ 40) እንደ ተመለከተው ከቅድመ ትምህርት ፈተና በልጦ የተገኘው የድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ (p<0.05) ሆኖ በመገኘቱ በአጭር ለቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የመጻፍ ችሎታን ያሻሻለ መሆኑን አመልክቷል። ይህም Collie, and Slater (1987)ስነጽሁፍ የቋንቋን የተለያዩ ተግባራት ለተማሪዎች ያቀርባል። ተማሪዎች የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢን በማንበብ ከበርካታ ምንባቦችና የቅንጫቢ አውድ ገጽታዎች ጋር እንዲለማመዱ ያደርጋል፤ የአረፍተ ነገሮችን አመሰራረት ተግባርና የተለያዩ የሀሳብ ማያያዣ መንገዶች ያቀርባሉ፤ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ይረዳል ከሚለው ሃሳባቸው ጋር የሚደጋገፍ ነው። እንዲሁም Hismongu, (2005) "ቋንቋን በስነጽሁፍ ማስተማር" በሚለው ጥናታቸው ተማሪዎችን ጽህፈት ለማስተማር የገፀባህሪያትን ማንነት በመጠቀም ያነሳቸውን አስተያየት በራሳቸው አገላለፅ እንዲጽፉ መርዳት ተመራጭ በመሆኑ የመጻፍ ችሎታን ለማጎልበት የሚረዱ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመተግበር ክሂሉን ማዳበር ይቻላል በማለት የገለጹትን ሃሳብ የሚደግፍ ነው።

የጥናቱ ሌላው ትኩረት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር በተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት ላይ ያለው ልዩነት መኖር አለመኖሩን የሚመለከት ነው።

የሙከራ ቡድኑ ትምህርቱን በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ መማራቸው ለመጻፍ እንዳነሳሳቸውና ፍላጎት ማጣትን እንዳስወገደላቸው ለመረዳት ተችሏል። እንዲሁም በማስተማሪያ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎቹ ውስጥ ያሉትን መልመጃዎች (ጥያቄዎች) በመስራታቸው እና ሰፊ ጊዜ ወስደው ተከታታይ ልምምድ በማድረጋቸው የመጻፍ ችሎታቸውን እንዲያሻሽሉና የመጻፍ ፍላጎታቸውን እንዲያጎለብቱ አድርጓል ወደሚል እሳቤ ያመጣል። ይህም (Hill, 1986) ስነጽሁፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ማካተት ለተማሪዎች ጠቅላላ እውቀት፣ አእምሯዊ ብስለት፣ ማህበራዊና ስነምግባራዊ እድገት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው። በተጨማሪም በስነጽሁፍቋንቋን ማስተማር እውነተኛ አውድን ስለሚፈጥርና ተማሪዎችን ስለሚያሳትፍ የቋንቋውን ትምህርት የተሳካ ያደርገዋል በማለት ከሰጡት ሃሳብ ጋር ይደጋገፋል።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ በማሻሻል፤ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ መሻሻል ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖሩ፤ እንዲሁም በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር ምክንያት የመጻፍ ፍላጎት ላይ ያለው ለውጥ ልዩነት መኖሩ፤ የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ ይህም የድህረ ትምህርት አማካይ ውጤት ከቅድመ ትምህርት አማካይ ውጤት በስታቲስቲክስ ጉልህ ሆኖ መገኘቱ አንድ አስረጂ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ በኩል በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን መማር የመጻፍ ፍላጎት ላይ ለውጥ መኖርና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን መማር የመጻፍ ፍላጎት ላይ ለውጥ አለመኖር ጉልህ ሆኖ መታየቱ ተጨማሪ አስረጅ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር፣ በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ከማስተማር በላይ የመጻፍ ፍላጎት በማጎልበቱ፣ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር ለመጻፍ ፍላጎት አዎንታዊ ተፅዕኖ አድርጓል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ ይመስላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ ሀሳብ

አስቀድሞ በተደራጁት ምዕራፎች የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መላምት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና የጥናቱ ወሰን፣ ተዛማጅ ጽሁፎች፣ ምርምሩ የተከተለው ስልት (ትዎሪ)፣ የተዛማጅ ጥናቶች፣ የጥናቱ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ትንተና፣ ገለፃዎችና ማብራሪያዎች በቅደም ተከተል ቀርበዋል። በመቀጠልም የጥናቱ ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና የመፍትሄ ሀሳቦች በጥናቱ ውጤት ላይ የተመሰረቱ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ለማቅረብ ተሞክሯል።

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን ሚና መመርመር ስለመሆኑ በቀዳሚ ምዕራፎች ተገልጿል። በዚህም መሰረት በጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው የታለሙት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ።

- በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ጽህፈት የተማሩ ተማሪዎች የተሻለ የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት አላቸውን?
- በአጭር ልቦለድ ጽፈትን በተማሩና ባልተማሩ ተማሪዎች መካከል የጽህፈት ችሎታ ልዩነት የላቸውም።

የጥናቱ ተሳታፊዎች በጅማ ዞን፣ በኦሞ ናዳ ወረዳ፣ በአሰንዳቦ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በ10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። የተማሪዎችን የናሙና አመራረጥ በተመለከተ በዚሁ የክፍል ደረጃ 587 ተማሪዎች በስምንት የመማሪያ ክፍሎች ተመድበው በመማር ላይ ይገኛሉ። በአንድ መማሪያ ክፍል ደግሞ በአማካይ 73 ተማሪዎች ይማራሉ። ጥናቱ በከፊል ሙከራዊ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ሁሉንም ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ማድረግ አልተቻለም። ስለዚህም አጥኚዋ ተማሪዎቹ የተመደቡት በችሎታ ስብጥር መሆኑና የአንደኛው ወሰነ ትምህርት አማካይ ውጤታቸው ተቀራራቢ መሆኑን ከውጤት ትንተና መዝገብ ካረጋገጠች በኋላ በእድል ሰጭ ንሞና ዘዴ ሁለት የመማሪያ ክፍሎች (10ኛ"B" እና 10ኛ"D")ተመርጠዋል። ከነዚህ ሁለት ክፍሎች ደግሞ በእድል ሰጭ ናሙና ዘዴ በመጠቀም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ተለይተው ለሙከራ ቡድን

ከተመረጠው ክፍል ተማሪዎች በቅድመ ፈተና የተሻለ ውጤት ያመጡ32 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

በጥናቱ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ሲሆን የክፍል ደረጃውን መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጽሐፍን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎችም ለማስተማር የተዘጋጁትን ይዘቶች (ጽህፈትን፣ ዘይቤዎችን፣ ገፀባህሪያትንና አንቀጽን) በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና ያለ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ (በተለመደው አቀራረብ) ከመማራቸው በፊት በቅድመ ትምህርት የመጻፍ ችሎታ ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ፈተናው በጥናቱ አማካሪና አጥኚዋ በምትሰራበት ትምህርት ቤት በሚያስተምሩ መምህራን ታይቶ ማስተካከያ ታክሎበት፣ በፓይለት ቴስት አስተማማኝነቱ ተገምግሞ የተማሪዎቹን የመፃፍ ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ቀጥሎም ለማስተማሪያነት የተዘጋጀውን የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ለአራት ሳምንታት ሲማሩ ቆይተዋል፡፡ በመጨረሻም ከቅድመ ትምህርት ፈተና ጋር አቻ የሆነ የድህረ ትምህርት ፈተና እንደ ቅድመ ትምህርት ፈተና ታይቶና ተገምግሞ ተግባራዊ በማድረግ ለጥናቱ የሚፈለገው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በተጨማሪም ተሳታፊዎቹ ለመጻፍ ያላቸውን ፍላጎት (ተነሳሽነት) ለመገምገም የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በፈተናና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭና ድምዳሜያዊ ስታቲስተክስ ተተንትነዋል፡፡

በፈተና አማካይነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻል ይረዳ ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም በቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤቶች መካከል በስታቲስቲክስ ጉልህ ልዩነት መታየቱ ($p<0.05$) የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እንደሚያሻሽል ለመረዳት ተችሏል፡፡ እንዲሁም ተሳታፊዎቹ በሞሉት የጽሁፍ መጠይቅ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ መማራቸው ለመጻፍ ያላቸውን ፍላጎት ላይ ለውጥ መታየቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት በማጎልበት ረገድ አዎንታዊ ተፅእኖ ይኖረው ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ተሞክሯል፡፡ ለዚህ የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ይህም በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር ምክንያት በተማሪዎች የመጻፍ ፍላጎት (ተነሳሽነት)

ላይ ልዩነት እንደሚያሳይ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ከጽሁፍ መጠይቁ ውጤትም የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በማስተማሪያነት በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት እንደሚያሻሽል (እንደሚጨምር) ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና ውጤት የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመጻፍ ፍላጎት ለማጎልበት ለተማሪዎች የሚቀርቡ የቋንቋ ትምህርቶች የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን መሰረት ያደረጉ (በአጋዥነት የሚጠቀሙ) ቢሆኑ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል አመልክቷል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

የጥናቱን ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ተችሏል፡፡

1. በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች እና የመጻፍ ችሎታ መሻሻል መካከል ግንኙነት አለ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ በቅድመ ትምህርቱ ያስመዘገቡት አማካይ ውጤት (23.88) በድህረ ትምህርት ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት (31.38) አንሶ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በመነሳት በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ መማር የመጻፍ ችሎታ እንዲሻሻል በማገዝ ረገድ ሚና አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡
2. በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በማስተማርና በተለመደው አቀራረብ በማስተማር የፈተናዎች ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ በተሰራው የባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት መሰረት የቲ-ዋጋ ከt-cri ዋጋ ልቆ ተገኝቷል፡፡ ይህም ቋንቋን በተለመደው አቀራረብ ከማስተማር በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ማስተማር ለተማሪዎች የመጻፍ ችሎታ መሻሻል እንዳስገኘላቸው ያረጋግጣል፡፡
3. በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ እና በተለመደው አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት በማጎልበት ረገድ ልዩነት ታይቷል፡፡ ይህምየአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ከተለመደው አቀራረብ በላይ የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት በመጨመር ረገድ ሚና እንዳለው ይጠቁማል፡፡

## 5.3 መፍትሄ ሀሳብ

በዚህ ጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶችና ማብራሪያዎች ተግባራዊ ለማድረግ ብሎም የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ለማሻሻልና የመጻፍ ፍላጎት ለማጎልበት እንዲቻል የሚከተሉት መፍትሄዎች ተጠቁመዋል፡፡

1. በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቋንቋን ማስተማር የመጻፍ ችሎታ መሻሻል ላይ የራሱ የሆነ ሚና እንዳለው በመገንዘብ መምህራን በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ በመጠቀም ቋንቋን ቢያስተምሩ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ ሊያሻሽሉ ይችላሉ።
2. የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ከተለመደው አቀራረብ በተሻለ መልኩ የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታና ፍላጎት የሚያሻሽል እና የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ-አሳታፊ የሆነ እንዲሆን ስለሚያስችል የቋንቋ መምህራን የቋንቋ ትምህርት አቀራረባቸውን በመፈተሽ ተግባራዊ ቢያደርጉ።
3. መምህራን በጥናት የተደረሰባቸውን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ወደፊት መሰል ጥናቶችን ቢያካሂዱ በመማር ማስተማር ሂደት የሚያጋጥመውን የተማሪዎችን የመጻፍ ማነስ እና የመጻፍ ፍላጎት ማነስ ችግር ሊያሻሽሉ ይችላሉ።
4. በጥናቱ ውጤት እንደተገለፀው በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችየተማሩት ተማሪዎች የመጻፍ ችሎታቸው መሻሻሉን ለማየትተችሏል። ስለዚህ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ሰፊ የመፃፍ ልምምድ እንዲያደርጉ የሚያስችል ሁኔታን ቢያመቻቹ።
5. የስርዓተ-ትምህርት አዘጋጆች በደረጃው በሚዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍት ውስጥ የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ከሌሎች ምንባቦች አንጻር ተመጣጥነው እና አሁን ካሉበት በቁጥር ተሻሽለው ቢቀርቡ የተማሪዎችን የመጻፍ ፍላጎት በማነሳሳት የመጻፍ ችሎታቸው የበለጠ ሊዳብር ይችላል።

## ዋቢ ጽሑፎች


ማረው አለሙ፡፡ (2003)፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡፡ አዲስ አበባ፤ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ አየለ፡፡ (2014)፡፡ የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ፡፡ ሐትፋም ትሬዲንግ ፒኤልሲ፡፡ አዲስ አበባ፡፡

አበራ ለማ፡፡ (1981)፡፡ አጫጭር ልቦለድ ታሪኮችና ሥነ-ግጥሞች፡፡ ኢትዮጵያ መጽሐፍ ድርጅት ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ወጋየሁ ተበጀ፡፡ (1980)፡፡ አጫጭር ልቦለድ ታሪክ፡፡ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፡፡ አዲስ አበባ፡፡

ዘመንፈስ ባራኪ፡፡ (1991)፡፡ "በስነ-ጽሁፍ አማካይነት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና"፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (2005)፡፡ የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን፡፡ አዲስ አበባ፡፡

……………….. (1998)፡፡ የስነ-ጽሁፍ መሰረታዊያን፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2004)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፀጋየ በየነ፡፡ (2004)፡፡ "የስነ-ጽሁፍ ቴክስቶችን በአማርኛ ቋንቋ ክፍል ውስጥ ስለመጠቀም የመምህራንና የተማሪዎች አመለካከትና አተገባበር" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

Adiamy,D.A. (2011). Approaes to composition writing. The case of junior secondary school Botswana Quarterly-international Journal Learning Development ISSN2164-4063.

https://pdfs.semanticscholar.org/.../96b68991f2bBfd6acbef17e6c0fbdd.

Ahmed sallal, I.(2014). The effect of using story on Reading Comprehension and Motivation for English Departement Students. Diyla University/ Iraq.

Black.c.and Manglers.J. 1995. Reason to Read. Thinking strategies for life Through literature. Orelt.col.org Module 5: Language through Literature.

Borja J.ojeda and Marina Torraibo. Literature in the English language classroom-poetry. www4,Ujaen.es/…/Literature%20in%20the%20language%20classroom..

Brufit, C.J. and Carter, R, A.(1986).Litrature and Language Teaching. Oxford: Universitypress.

www.journals.aiac.org.au/index.php/IJALEL/article/view/1108

Calvert, L. (2004) A Teachers' Guide to the Signet Classics. Edition of charlcs Dikens Great Expectation, Pengun Group (U.S.A)

Carter R and Long, M.N.(1991). Teaching Literature. London, Long man Group Ltd.https://www.iiste.org/Journals/index.php/JAAS/article/.../12419

Chaistan, K. (1988). Devloping Second Language Skills: Theory and Practice. SanDiego: Harcourt Brace Jovanouich.

Clark,IL. (2003). Concepts in composition Theory and practice in the teaching writing Lawarence Enabaum Associates pulishers. Machwa Newjersy,London.

www.library.uc.edu.kh/.../1.Concepts%20in%20composition%20%20theory%20and2

Colli, J. and Slater. (1987). Literature in language classroom; A recourse Book of ideas and Activities.Cambridge University press.

https://searchworks.stanford.edu/view/1293626

Fischer, S. R. (2003). A History of Reading. London: Reaktion Books Ltd

Graham, S. and Perin D(2007). Writing Next, Effective Strategy to improve Writing of Adolcent in Middle and High school. Carnegie Corporation. New York.

https://www.carnegie.org/media/.../ccny report 2007 writing.pdf

Hedge.J (1988).Writing. London. Oxford University press.

https://www.nepjol.info/index.php/NELTA/article/dowbload/.../3823

Hill, Jennifer (1986) Teaching Literature in language classroom.Maenillan.

Idge university press. Journals.euser.org/index.php/ejls/article/view/617/606

Hismongu, M. (2005) Teaching English Through Literature. Journal of Language and Linguistic Studies.vol.1,No -1.

www.jlls.org/index.php/jlls/article/viewFile/6/7

Hasen, E. (1993). The double role of fiction in foreign language teaching Towards a creative methodology in selected articles from the English teaching forum.By Thomas ed.Washington DC. US/A

Kavaliauskiene, G. (2009)." Role of the mother tongue in learning. English for specific purposes world.

Knatib, M. "etal".(2012). Literature and Language Teaching. Journal of

Malakneh Mengistu (1999). Fundamental of Literature for college,A.A Birhan P.E

Mekay, S. (1986)."Literature in the ESL Classroom." In C.J.Brumfit, C.J. and R.A. Carter (edrs). Literature and Language. Hong kong: oxford university Press.https://files.eric.ed.gov/fulltext/ED481411.pdf

Raims.ann. (1983).Techiques in teaching writing. Oxsford.Oxsford university Press.https://global.oup.com/.../techniques-in-teaching-writing-9780194341

Richards, J. C.(1971)."Anon-contrastive approach to Error Analysis." English Language Teaching Journal.

Thom.N.T (2008).Using Literary Texts in Language Teaching.VNU. Journal Of Science Freign Language.V.24 pp 120

https://knepublishing.com/index.php/Kne-Social/article/view/.../4286

Venkates,W. (1997). Principle of teaching English Delhi printed at modern Printer.

Widowson, H. (1982). The use of Literature. Henis, Mary and Wiliam Ruther Ford.On TESOL 81 Washington D.C. https://www.jstor.org/stable/3586672

Williams, J.D. (2003). Preaparing to teach writing research theory and Practice. (3rded.)

https://www.amazon.com/Preparing-Teach-Writing-Research-Practice

Yavus, A. (2010). Inhancnig Creativity in the Comunicative Language Class Room Through Poetry as Litrary Genry. Temmuz. Augstos-Eyali/ Dil Dergisi.sail:149.

Yeasmin, N.etal (2011). Teaching Language through Literature; Desig Appro Priate classroom Activities. ASA University Revew, vol.5 No.2, December

Zamel ,V. (1982). Writing the process discovering meaning. TESOL.www.jlls.org /index.php/jills/article/…? Journal of language and Linguistic studie

www.cscanada.net/index.php/sll/article/view/4277

**አባሪ "ሀ"፡- የቅድመ ትምህርት ፈተና**
**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

**ቅድመ ትምህርት ፈተና**

የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታቸውን ለመመርመር የሚያገለግል ፈተና

መለያ ቁጥር ……… ክፍል ……… ምድብ ………..

የተፈቀደው ጊዜ፡- 1፡30

**አጠቃላይመመሪያ**፡- የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመመርመርለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት በመረዳት፤ የምንባቡን ሀሳብ በራስ አገላለጽ ለመግለጽ የሚያስችሉ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ፣ በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

ምንባብ

## የእርግቦች ፀሎት

በሰፊው መስክ ላይ እረኛው የዕለት ሳራቸውን ይግጡ ዘንድ በጎቹን በማለዳ አሰማርቷቸዋል፡፡ ከተሰማሩት በጎች መካከል ባለ ግልገል የሆነችው እናት በግ፤ ግራ ቀኙን አልፎ አልፎ በንቃት እየቃኘች ግልገሏን በግጦሽ መስኩ ላይ ትመራለች፡፡

በተመሳሳይ ሰዓት ከላይ ሰማይ ግዛቱ የሆነና ሌቱን በርሃብ ያሳለፈ ግዙፍ ንስር ከላይ ቁልቁል ተመለከታቸው፡፡ የራበው ንስር አይኖች ውስጥ የገባችው ትንሿ ግልገል ናት፤ግልገሏ አሁንም ትግጣለች፡፡ ሰፋፊ ክንፎቹን ዘርግቶ ጥፍሮቹን እየሳለ የራበው ንስር ከላይ ከሰፊው ሰማይ ቁልቁል መምዘግዘግ ሲጀምር አላዩትም ነበር ቀና ብለው፡፡

በተመሳሳይ ሰዓት፤ ከሌላ አቅጣጫ ሌላ የራበው ንስር ግልገሏን በንስር አይኖቹ ተመልክቶ ነበርና ያደረበት ርሃቡን ለማስታገስ በሙሉ ኃይሉ አየሩን ቁልቁል ሰንጥቆ መብረር ጀምሯል፡፡ ድንገት በዞርታቸው ሲተያዩ ንስሮቹ ወደ ምድር የሚያደርጉትን በረራ በስግብግብ ንዴት አቋርጠው ከአደናቸው አናት ላይ እርስ በእርስ መፋለም ጀመሩ፡፡

ሁለቱንም ክፉ ርሃብ ቀፍድዶ እያንገበገባቸው ነበርና በምህረት አልባ ጥፍሮቻቸው ሊዘናጠሉ ቸኩለዋል፡፡ ከግጦሹ ሜዳ ያለችውን ግልገል የግል ለማድረግ በሹል ጥፍሮቻቸው የሞት ሽረት ጦርነት ውስጥ ገቡ፡፡

ልጅ ግልገል ቀና ብላ ተመለከተችና እናቷን፦
"እማዬ የሰማይ ወንድሞቻችን ምን ሆነው ነው የሚጣሉት? ..." ስትል ጠየቀቻት፡፡
እናት መለሰችላት ዕድሜዋን በሚመጥን አነጋገር፡፡ "... ልጄ ሆይ ለምን እንደሆነ በእርግጥ እኔም አልገባኝም፡፡ ግን የሰማይ ወንድሞቻችን መሀል ሰላም እንዲወርድ በንፁህ ልብሽ ፀልይላቸው፡፡..." አለቻት፤ እናትም ቀና ብላ እየተመለከተች፡፡ የንስሮቹ ሰፋፊ ክንፍ ጥላው የግጦሹ ሜዳ ላይ እንደ ደመና ግርዶሽ ከብዶ እየተበታተነ ይታያል፡፡

ግልገሊቱ በግ ለእናቷ ምክር በንፁህ ልቧ ምላሽ ሰጠች፡፡ "...አምላኬ ሆይ የሰማይ ወንድሞቻችንን ፀብ ተመልከት፡፡ የሰላም አባት ነህና ሰላምም በመካከላቸው አውርድ እባክህ፡፡ አሜን!..." አለች፡፡

ከላይ ንስሮቹ በመናከሳቸው በርትተዋል፡፡ ጥፍሮቻቸውን አሹለው እየተናጩ ነው፡፡ የፀባቸው ማብቂያ መቼነቱ በውል አይታወቅም፡፡ መገመትም ከባድ ነበር፡፡ የፍልሚያው አሸናፊ ግን ድሉን የሚያከብረው የበጊቱን ግልገል በማጣጣም ነው፡፡ አልያም እናቲቱን ይሆናል፡፡

ምንጭ፦ ተስፋዬ አየለ 2014 ዓ.ም

***መመሪያ አንድ፦ ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡ 30%***

1. በታሪኩ ውስጥ ያለችው ባለግልገል እናት በግ ምን እንዳደረገች ግለፁ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………

2. በንፁህ ልቦና ምላሽ የሰጠችው ገፀባህሪ ማንነት እና የሰጠችውን ምላሽ ፃፉ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………….
……

3. በዚህ ምንባብ ውስጥ በዘይቤ የተገለፁ አረፍተ ነገሮችን (ሀሳቦችን) ዘርዝሩ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………
………………………………………………

4. በተመሳሳይ ሠዓትና በተለያየ አቅጣጫ የመጡት እነማን እንደ ሆኑና ለምን እንደመጡ ግለፁ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………

5. ምንባቡ በአጠቃላይ ስንት አንቀፆች አሉት?

……………………………………………………………………………………………

6. አንቀፅ ሶስት የተገነባበት ዓረፍተ ነገር ብዛት ፃፍ፡፡

……………………………………………………………………………………………..

7. ግልገሊቱን በግ እና እናቲቱን ያስፈራቸው ነገር ምን ነበር? ግለፁ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………..

8. የበጊቱን ግልገል ማጣጣም ነው ሲል መልዕክቱ ምን ለማለት እንደሆነ አብራሩ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………
……………………………………………

9. ከአዳናቸው አናት ላይ ያንዣብባሉ የሚለውን በራሳችሁ አገላለፅ ግለፁ፡፡

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………..

10. የዚህ ምንባብ ፍሬ ሀሳብ ምንድን ነው?

……………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………

**መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው የተዘበራረቀ ሲሆን ምንባቡን መሠረት በማድረግ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡ 10%**

11. ግልገሏን የግል ለማድረግ በጣም ተቻኩለዋል፡፡

12. ከሌላ አቅጣጫ የራበው ንስር ቁልቁል መብረር ጀመረ፡፡

13. ግዙፍ ንስር ከላይ ቁልቁል ተመለከታቸው፡፡

14. እረኛው በጎቹን በማለዳ ወደ መስክ አሰማርቷቸዋል፡፡

15. የሠላም አምላክ ነህና ሠላምን አውርድ፡፡

………………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………………
………………………………………………………………………………………

**መመሪያ ሦስት፡- ከዚህ በታች ባሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ፃፍ/ፊ፡፡10%**

16. ግራ ቀኙን በንቃት <u>እየቃኘች</u>ሣር ትግጣለች፡፡

………………………………………………………………………………………………

17. በሰፊው <u>መስክ</u> በጎቹን አሰማርቷል፡፡

………………………………………………………………………………………………

18. ከሠፊው ሠማይ <u>ቁልቁል በመምዘግዘግ</u> እንዳለ ተመለከተች፡፡

………………………………………………………………………………………………

19. የወንድሞቻችንን <u>ፀብ</u> አብርድልን፡፡

………………………………………………………………………………………………

20. ድንገት <u>በዞርታቸው</u> ሲተያዩ ተገናኙ፡፡

………………………………………………………………………………………………

አባሪ "ለ"፡- የድህረ ትምህርት ፈተና

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

**ድህረ ትምህርት ፈተና**

የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ችሎታቸውን ለመመርመር የሚያገለግል ፈተና

መለያ ቁጥር ……… ክፍል ……… ምድብ ………..

የተፈቀደው ጊዜ፡- 1፡30

**አጠቃላይመመሪያ**፡- የዚህ ፈተና ዋና ዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የተማሪዎችን የመጻፍ ችሎታ እና ፍላጎት ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመመርመርለታሰበው ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ የምንባቡን ቀጥተኛ መልዕክት በመረዳት፤ የምንባቡን ሀሳብ በራስ አገላለጽ ለመግለጽ የሚያስችሉ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ የሚጠይቁ፣ በቀጥታ የሚመለሱ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

ምንባብ

## ሞገደኛው ነውጤ

"ስምህ?" እንዳቀረቀሩ ጠየቁት ዳኛው፡፡ "ነውጤ ደስታ - " መልስ ሰጠ - ተረጋግቶ፡፡ "እድሜህ?" አሉና ቀና ብለው የጎድን አስተዋሉት፡፡ "ደጃች ገለታ ኦርቾ ለብአ ኢየሱስ ላይ ግብር ያጋቡለት ነው ይላሉ የተወለድኹት፡፡ እንግዲህ ዘመኑን ያስሉት - የትናየት መሰለዎት፤ ሩቅ ነው! ሩቅ …" እንደ ሚያሰላ ሰው አመልካች ጣቱን በጆሮ ግንዱ ላይ ደግኖ መለሰላቸው፡፡

"አመተ - ምህረቱን አታውቀውም?" ፊት ለፊት በጥያቄአቸው አፈጠጡበት፡፡ "ምን - የምህረት ዘመን አንጼ ይመጣል፤ አንጼ ይሄ ዳል - ምን ተይዞ ብለው ነው ጌታው? ሲለው አዝመራው የሰጠ ይሆናል - ሲለው ውርጩና አረሙ በቡኣያው ያስቀረዋል፡፡ ምኑ እጡ ብለው ነው! …" አለና ይቅርታ ድምፀት አሰማ፡፡

"ባማርኛችን አልተግባባንም መሰለኝ - እኔ ያልኩህ …" ሲሉ አቋረጣቸው ተከሳሹ ነውጤ፡፡ "እርግ! እርግ! …ይጫወቱ! ከከተማ ሰው ጋር መጨዋወትን እንዲያው ታንጀቴ ነው - የምወደው፡፡" "አቶ ነውጤ ለምትጠየቀው ጉዳይ ብቻ መልስ ስጥ! - አድራሻህ?" "ፌጥራ - መርሃቤቴ፡፡ " ስራህ?" "ግብርና - " ለምን እንደተከሰስክ ታውቃለህ?" "ማ እኔ?" ጥያቄው ለሱ

እንደሁ የተጠራጠረ መሰለ፡፡ "አዎ አንተ …" "እኔ? … ለምን እንደተከሰስኩ?" "አዎን አንተ …" "የለም-አላውቅም፡፡"ፍርጥም ባለ አነጋገር መለሰ፡፡ "ነፍስ አላጠፋህም?" ሆነ ብለው ወንጀላቸውን እንደሚክዱ ተከሳሾች ሁሉ፤ የነውጤም አዝማሚያ ወደ ዚያው ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት የወሰዱት ዳኛ፤ የምፀት ፈገግታ አሳዩ፡፡

"ነፍስ? የምን ነፍስ? ስብሃት ለአብወወልድ!" ነውጤ መሀል አናቱን የተመታ ያህል በድንጋጤ ወከክ አለ፡፡ "የሰው ነፍስ - " እረ በፍጹም! እንኳን የሰው ነፍስ የጫጩትም ያሳዝነኛል - በስማም …" አሁንም ድንጋጤው አለቀቀውም - መስቀለኛ አማተበ፡፡

"ተፈራ አደፍርስን አልገደልክም?" ዳኛው እንደ መቆጣት አሉ፡፡ "ተፈራ ሞተ እንዴ? …ወይኔ ወንድሜን! ወይኔ! …" እራሱን በጆቹ ይዞ መጮህ ሲጀምር፤ ዳኛው አቋረጡት፡፡ "እንዳይሞት አድርገህ ኖሯል እንዴ የገደልከው?" በምፀት ሳቅ አሉ፡፡ "እረ አልገደልኩትም! መሞቱንም ገና ከርስዎ መስማቴ ነው - ወይኔ! ወይኔ ወንድሜን! ወይኔ አብሮ አደጌን! ወይኔ! ወይኔ! …ለመሆኑ የት ነው የሞተው?" አለና ካንጀቱ ስቅስቅ ብሎ ማልቀሱን ተያያዘው፡፡

"ለተጠየከው ጥያቄ በትክክል መልሱን ስጥ! ምን ታመረታታለህ?" ተከሳሹ የሚያፌዝባቸው መሰላቸውና የምር ተቆጡ፡፡ "ጌታዬ! አብረን አፈር ፈጭተን - ውሃ ተራጭተን ባንድ ቀዬ ያደግን ነን እኮ - እውነትዎን ነው እንዴ የሚሉኝ? እውነት ተፈራ ሞተ? የት ነው የተቀበረው? ወይኔ ተፈራ! ወይኔ ተፈራ! ወይኔ ጓዴን! …" በፍርድ ቤቱ ውስጥ እየዬውን አቀለጠው፡፡ "አትጨህብን! …ለመሆኑ ወንጀሉን ለመፈጸም ያነሳሳህ ምክንያት ምን ድነው? የእለት ወይስ የቆየ ግጭት ነበራችሁ?" ዳኛው ወደ ጉዳዩ ጭብጥ ቶሎ ለመሸጋገርና ተከሳሹ የዘየደውን የማምለጫ መንገድ ለማሰናከል የነቁ መሰሉ፡፡

"አዬ ጌታዬ! - እሱንስ አያንሱት - ያኔ፣ ያኔ ጠላት አገራችንን በወረረበት ዘመን፣ በገና ጨረኣ ሩር ስንጫወት፣ ነፍሱን ይማረውና ከወሰን ጋር ክፉኛ ተጋጭተው ተፈራ ባፍና ባፍንጫው ደም ሲተፉ፣ ተሸክሜው ከቤት ያገባሁትና ነፍሱን ያተረፍኩት እኔ ነበርኩ-ዋ ምን ያደርጋል! የልጅነት ጓደኛ ትዝታው ብዙ ነው፡፡ …አሁን እውነት ተፈራ ሞተ ነው የሚሉኝ? …ወይኔ ተፈራ! ወይኔ ጓዴ! ወይኔ! ወይኔ! …" "መልሰህ እኔኑ ትጠይቃለህ?" በንዴት የንባብ መነፅራቸውን ከጠረጴዛው ላይ ወርወር አደረጉት - ዳኛው፡፡ "ይእርታ! - ይእርታ ጌታዬ፡፡ ለመሆኑ ምን ነክቶት ነው የሞተ? ወይኔ ጓዴን! ወይኔ ተፈራ! ወይኔ! ወይኔ! …" ነውጤ እራሱንና ወገቡን አፈራርቆ በጆቹ እየያዘ እዬየውን አቀለጠ፡፡

"ምን? ...ምንድነው የምታምታታው? ...ማነህ ስነ ስርአት አስከባሪ ና አውጣልኝ ከዚህ! አእምሮው የተነካ መሆን አለበት - አማኑኤል ተልኮ የምርመራው ውጤት የዛሬ ሳምንት ከፋይሉ ጋር ተያይዞ እንዲቀርብልኝ!" ሲሉ በቁጣ የቀሉ ድፍርስ አይኖቻቸውን እያጉረጠረጡ ትእዛዝ ሰጡ። ሲቆጡ የሰው ቀልብ ይገፋሉ። "ወይኔ ተፈራ! ወይኔ ጓዴ! ወይኔ ዡግናው! ወይኔ ቶክቻው! ወይኔ! ወይኔ! ..." እያለ በስነ ስርአት አስከባሪው እየተገፈተረ ወደ ማረፊያ ቤት ተወሰደ። በሁኔታው ያልተደናገጠ ሰው አልነበረም።

ምንጭ:- አበራ ለማ (1981) አጫጭር ልቦለድ ታሪኮችና ሥነ-ግጥሞች

**መመሪያ አንድ:- ከ1-10 ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ ስጡ። 30%**

1. ከምንባቡ እንደምንረዳው ነውጤ ደስታ ምን አይነት ሰው ነው?

..........................................................................................................

..........................................................................................................

2. በአማርኛችን አልተግባባንም ያለው ማነው?

..........................................................................................................

3. ነውጤ አናቱ የተመታ ያህል የደነገጠው ለምንድነው?

..........................................................................................................

...............................................

4. ተፈራ አደፍርስ የተባለው ሰው ማነው?

..........................................................................................................

5. የተፈራ አደፍርስን ሞት ለነውጤ የነገረው ማነው? የትስ ነው?

..........................................................................................................

........................................................................

6. ወደ አማኑኤል የተላከው በማን አማካኝነት ነው?

.......................................................................................................

7. በምንባቡ ውስጥ ስንት ገፀ-ባህሪያት አሉ?

………………………………………………………………………………………………

8. አንቀጽ ስምንት ስንት አብይ እና ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች አሉ?

………………………………………………………………………………………………

9. ነውጤ ከአንጀቱ ስቅስቅ ብሎ ያለቀሰው ምን ሆኖ ነው?

………………………………………………………………………………………………

10. የአንቀጽ ስድስትን ሙሉ ሀሣብ በአንድ ዓረፍተ ነገር ግለፁ፡፡

………………………………………………………………………………………………

**መመሪያ ሁለት፡- ከ11-15 በተሠጡት አረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት ዓውዳዊ ፍቺ ስጡ፡፡ 10%**

11. ሲለው አዝመራው<u>**የሠጠ**</u> ይሆናል፡፡

………………………………………………………………………………………………

12. ዳኛው <u>**የምፀት**</u> ፈገግታ አሳዩ፡፡

………………………………………………………………………………………………

13. ውሃ ተራጭተን በአንድ <u>**ቀዬ**</u> ያደግን ነን፡፡

………………………………………………………………………………………………

14. ወደ <u>**ማረፊያ ቤት**</u> ተወሠዱ፡፡

………………………………………………………………………………………………

15. የነውጤ <u>**አዝማሚያ**</u> ወደ እዛው ነው፡፡

………………………………………………………………………………………………

**መመሪያ ሦስት፡- ከ16-20 ያሉት አረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቆ የቀረቡ ሲሆን አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡ 10%**

16. ጫኔ ተፈራ አደፍርስን እንደገደለው በተነገረው ጊዜ አለመግደሉን ተናገረ፡፡

17. ለምን እንደተከሰስኩ አላውቅም ነብስም አላጠፋሁም አለ፡፡

18. በስተመጨረሻም ነውጤ በስርአት አስከባሪ ወደ ማረፊያ ቤት ተወሰደ፡፡

19. ነውጤ ሙሉ ስሙን፣ የትውልድ ዘመን እና ቦታውን ተጠይቆ ተናገረ፡፡

20. ነውጤና ተፈራ አደፍርስ አብሮ አደግ መሆናቸውን ተናገረ፡፡

……………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………

……………………………………………………………………………………………………

………………………………………………………………………………………

## አባሪ "ሐ"፡- በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሒማኒቲስ ኮሌጅ አማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል**

**ድህረ ምረቃ ፕሮግራም**

**የመፃፍተነሳሽነትመለኪያመጠይቅ**

የአስረኛክፍልተማሪዎችንየመፃፍ ተነሳሽነትመለኪያመጠይቅ

ውድተማሪዎች፡- የዚህመጠይቅዋናዓላማ በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎች ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል እና ፍላጎትን ለማዳበር ያለው ሚና፣ በ10ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ለሚካሄድ ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ አላማአይውልም፡፡ የአንተ/ቺ ትክክለኛ ምላሽ የጥናቱ ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ስለሆነም የምትመልሳቸው/ሻቸው ምላሾች የራስህን/ሽንፍላጎት በትክክል የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ጥያቄዎችን በትዕግስት አንብበህ/ሽ ምላሽ በመስጠት ለምታደርግልኝ/ጊልኝ ቀናት ብብር በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

ክፍል……….. መማሪያ ክፍል…..…… መለያ ኮድ ……….

ማሳሰቢያ፡- ሀ. የትኛውንም መልስ ብትሰጥ/ጭ ትክክል ወይም ስህተት አለመሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ አስገባ/ቢ

ለ. ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ ጥያቄዎችን መመለስ አይፈቀድም

ሐ. ለምላሽህ/ሽ መነሻ የምታደርገው/ጊው ከአሁን በፊት (ይህጥናት ከመካሄዱ በፊት) የነበረህን/ሽን የመፃፍ ልምድና ተግባር እንጂ ወደ ፊት ይኖረኛ ልብለህ/ሽ የምታስበውን/ቢውን አይደለም፡፡

***መመሪያ፡-*** በሰንጠረዡ ውስጥ ለቀረቡት 10 ጥያቄዎች እያንዳዳቸውን አዎ /አይ አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ በምትመርጠው/ጪው አማራጭ ትይዩ ይህን"X" ምልክት አድርግ/ጊ፡፡

| ተ.ቁ | የጽሁፍ መጠይቆች | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎ | አይ |
| 1 | ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን ትምህርት በጥሞና በመከታተል ይሳተፋሉ? | | |
| 2 | መምህሩ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ እና አላማ በጥቁር ሠሌዳ ላይ ፅፈው በሚያስተዋውቁበት ጊዜ በጥሞና ይከታተላሉ? | | |
| 3 | መምህሩ ያለፈውን ትምህርት በማስታወስ ወደእለቱ ሲሸጋገር ለሚጠይቀው ጥያቄዎች ተማሪዎች ምላሽ ይሰጣሉ? | | |
| 4 | በትምህርቱ ላይ ተማሪዎች በጥንድ እና በቡድን በመወያየት ሀሣብን ይሰጣሉ? | | |
| 5 | መምህሩ ስለዕለቱ ትምህርት ርዕስና ይዘት የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ማብራሪያ ሲያደርጉ ተማሪዎች በመከታተል ማስታወሻ ይጽፋሉ? | | |
| 6 | ለማስተማሪያነት የተዘጋጀውን የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ለተማሪዎች በማዳረስ በውስጡ ያሉ መልመጃዎችን እና ድርጊቶች በፅሁፍ እንዲያቀርቡ ያበረታታሉ? | | |
| 7 | መምህሩ ተማሪዎች የተሰጣቸውን የግል፣ የቡድን እና የጥንድ ሥራን መስራታቸውን በመከታተል ለሚፅፉት መልስ ድጋፍ ያደርጋሉ? | | |
| 8 | በመምህሩና በተማሪዎች፣ በተማሪዎችና በተማሪዎች መካከል አዎንታዊ የሚባል መስተጋብር አለ? | | |
| 9 | በክፍል ውስጥ የሚካሄደው የመማር ቆይታ ሰፊውን ጊዜ ለተማሪዎች የመጻፍ ልምምድ ተሰጥቷል? | | |
| 10 | በሚሰጠው ትምህርት ላይ ተማሪዎች ግልጽ ያልሆነላቸውን ጠይቀው ይረዳሉ? | | |

11. ለማስተማሪያነት የተዘጋጀውን የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ውስጥ ያሉትን ተግባራት በፅሁፍ በሚያቀርቡበት ጊዜ የተማሪዎቹ የግል ተሳትፎ ምን ይመስላል?

…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………..

12. በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ሲማሩና በሌላ ዘዴ በሚማሩበት ጊዜ ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………………
…………………………..……………………………………………….

አባሪ "መ"፡- የማስተማሪያ አሀድ

በአጭር ልቦለድ ቅንጫቢ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂልና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለውን ሚና ለመመርመር ለተሰራ ምርምር የአጭር ልቦለድ ቅንጫቢዎችን ተጠቅሞ ለማስተማር የተዘጋጀ የማስተማሪያ አሀድ፡፡

ይህ የመማር/ማስተማር አሀድ፣ Chaistan,K.(1988) የመፃፍ ችሎታ ማደግ ያለበት መሰረታዊ የተግባቦት ክሂል በመሆኑና በየትኛውም የሙያ መስክ ተፈላጊ ክሂል ሲሆን፤ ለክሂሉ መዳበር የተሻለ የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥና የተማሪዎች ችሎታ እንዲዳብር ማገዝ የመምህር ድርሻ መሆኑን በገለጸው መሰረት፣ ይዘቱ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍና መርሀ ትምህርት መሰረት በማድረግ ነው የተዘጋጀው፡፡ ጽህፈትን፣ አንቀጽን፣ ዘይቤዎችንና ገፀባህርያትን በትምህርት ይዘትነት በመምረጥ ለማስተማር የቀረበ ሲሆን፤ ተማሪዎች ለተመረጡ የትምህርት ይዘቶች ከቀረበላቸው ቅንጫቢ ጽሁፍ (ምንባብ) በመነሳት ከምንባቦቹ ለወጡት የተለያዩ ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ትምህርቱ የተሰጠው ከሚያዚያ 10/08/2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 4/09/2015 ዓ.ም ለአራት ሳምንታት ከሰዓት በኋላ ዘወትር ማክሰኞና ሮብ ሲሆን ሰአቱ፣ 8፡00 እስከ 8፡40 አንዱ ቡድን ሲማር፤ ከ9፡00 እስከ 9፡40 ሁለተኛው ቡድን በቀን ለ40 ደቂቃ ሲማሩ ቆይተዋል፡፡

የመማሪያ ቦታ፡-በትምህርት ቤቱ ባለው የመማሪያ ክፍል፤

መምህር፡-ዘሪሁን በቀለ፡፡

የትምህርቱ አጠቃላይ አላማዎች፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- ከቀረቡት አሀዶችና አስረጂዎች በመነሳት የመፃፍ ምንነትና አገልግሎት ይገልፃሉ፡፡
- ከሚያደርጉት ውይይትና ልምምድ በመነሳት ርዕስ በመምረጥ አንቀጽ ይጽፋሉ፡፡
- ከቀረቡት አስረጂዎችና ልምምዶች በመነስት የዘይቤ አይነቶችን ይጽፋሉ፡፡
- ከቀረቡላቸው የልምምድ ተግባራት በመነሳት ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታና ፍላጎት ያጎለብታሉ፡፡

## ክፍለ ትምህርት አንድ፡- መጻፍ

- በዚህ ክፍለ ትምህርት የመጻፍ ምንነት፣ የመፃፍ አገልግሎት እና የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የሚያስችሉ ዘዴዎች ይቀርቡበታል፡፡

- ትምህርቱ የተመደበለት ጊዜ 1፡20 ሰዓት

- የትምህርቱ ዓላማ፡- ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች

- የመፃፍ ክሂል ከሌሎች ክሂሎች ልዩ የሚሆንበትን ምክንያት ያብራራሉ፡፡
- የመፃፍን አገልግሎት ይገልፃሉ፡፡
- ስለተለያዩ የየዕለት ገጠመኞቻቸው ይፅፋሉ፡፡

ምንባብ

## የአንድ ጎን መኝታ

የአባቴ ጥቁር አለንጋ በቤታችን ሶስት አይነት ስም ነው ያላት፡፡ ገላምጤ እንላታለን፤ ጥፋት ስናጠፋ የምትገላምጠን አድርገን ስለምንወስድ፡፡ ጠንቋዬ እንላታለን፤ ከአባታችን ተሰውረን የምንፈፅመውን ጥፋት እንደምትነግርብን በልጅነት ልባችን ስለምናምን፡፡ መንጌ እንላታለን በድብቅ፤ ኮስተር ያለች መልክ ጥቁር ስለሆነች፤ ስርዓት ሲርቀን ቅጣቷ ስለሚያንቀጠቅጠን፡፡

የአባቴ ጥቁር አለንጋ የቤታችን ክብርት እመቤት፤ የቤተሰባችን ስርዓት መሪ ዛሬም ከልጅነት ትዝታዎቼ መካከል ናት፡፡ የልጅነት ማንነቴ አክሊል ነበረችና ወጣትነቴ ከቶ ሊዘነጋት አይችልም፡፡ የቀጥታው መንገድ ተጠሪ፤ ማፈንገጥ ሳስብ ወደ አባቴ ህጎች የምትመልሰኝ መሪዬ ናት፡፡ **ትምህርት**፤ …**ጥናት**፤ …**ስርዓት** የሚሉ ኮስታራ የአባቴ ቃላት የታተሙባት ቅቤ የጠጣች ጥቁር ጉማሬ፡፡ ከተሰቀለችበት ሳትወርድ ልጅነቴን ቀጥ አድርጋ የገራች የአባቴ ታዛዥ ስርዓት አስከባሪ፡፡

በአባቴ ጥቁር አለንጋ እየተቃኘሁ በግብረ-ገብነት ባድግም መንግስት ከፃፈልኝ የተራ ዜግነት እጣ ግን መትረፍ አልቻልኩም፡፡ የአባቴ ጥቁር አለንጋ የገነባችውን ሁሉ አፍርሶ በፈለገው መንገድ የዘወረኝ በዕውቀት ያልተገራ የተራ ስግብግቦች ስብስብ፤ የአንድ ተረታም ፓርቲ ተልካሻ

ስርዓት ነው፡፡ ተምሬ፤ ተመርቂ ያለምኩትን ሳይሆን በደመነፍስ ያለመልኝን እንድኖር የሚጠመዘዝ ሀገራዊ ስርዓት፡፡ ስለዚህ ሰካራም ሆንኩ፡፡ ከሰካራምም ተምሮ የተማረረ ሰካራም፡፡

ምንጭ፡- ተስፋዬ አየለ 2014 ዓ.ም

መመሪያ አንድ፡- ከ1-5 ያሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በጽሁፍ መልሱ፡፡

1. የባለታሪኩ አባት ምን አይነት ሰው ናቸው?

…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
……

2. የባለታሪኩ አባት አለንጋ ስሞች ምን ምን ናቸው?

…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
……

3. የባለታሪኩ አስተዳደግ ከግብረ-ገብነት አንፃር እንዴት ይገለፃል?

…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
……………………………………………

4. ባለታሪኩ የአባቱን አለንጋ በአሉታዊ ወይስ በአዎንታዊ ነው የሚያስታውሰው? እንዴት?………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………

5. ባለታሪኩ የተገነባበትን ግብረ-ገብነት ያፈረሰው ምንድን ነው?

…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
……………………………………………………………………………………

መመሪያ ሁለት፡- ከዚህ በታች ተዘበራርቀው የቀረቡ አረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተላቸውን አስተካክላችሁ በአንድ አንቀጽ ፃፉ፡፡

1. በመጨረሻም ቤተሰቡ እንዲበሉ አቀረበች፡፡

2. በመጀመሪያ ምግቡን ለማዘጋጀት የሚሆኑ ግብአቶችን አዘጋጀች፡፡

3. የበሰለውንም ምግብ በመመገቢያ ሳህን ላይ አደረገችው ፡፡

4. ሲፈን ለቤተሰቧ ምግብ ለማዘጋጀት ፈለገች።

5. ከዚያም የተዘጋጁትን ግብአቶች በትክክለኛ መጠን እና አበሳሰል አበሰለች።

…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………………………………………………
…………………………………………………

ክፍለ ትምህርት ሁለት፦ ዘይቤያዊ አገላለፅ

በዚህ ክፍለ ትምህርት የገፀ-ባህሪ ምንነትን እና ስለልቦለድ ምንነት ይገለፅበታል።

ለትምህርት የተመደበ ጊዜ 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፦ ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፦

- የልቦለድን ምንነት ይገልፃሉ።
- የገፀባህሪን ምንነት ያብራራሉ።
- በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ገፀባህሪያትን ለይተው ይፅፋሉ።
- የልቦለዱን መሪ እና ንኡስ ገፀባህሪያት ይገልፃሉ።

ምንባብ

**ሐሊማ፤ ሽሪፎን ያገባች ዕለት**

"ሆዬ፤ የምትይውን ክታብ አላስርም እኔ።" "ዶቃው ብቻ ምኑን ጌጥ ይሆናል ብለሽ ነው ልጄ! ክታብሽ ከብቶችሽ እንዲረቡ፤ ባልሽ በጠላት እጅ እንዳይወድቅ፤ ብዙ ልጆች እንድትወልጂ፤ የወለድሻቸው ልጆች እንዲባረኩ ይረዳሻል። እንዲያውም ዕድለኛ ነሽ አንቺ። በቀዬአችን ሠርግ ሳናይስንት ጊዜ አለፈ።። ሰው ሁሉ ሠርግ ናፍቆታል። ሊያይሽ የሚመጣው ብዙ ነው። ክታቡ ከክፉ ዐይንም ይጠብቅሻል" እያለች የሐሊማ እናት፤ ከዲጃ፤ እምቢታዋን ለማስተው ታግባባት ጀመር።

"ሆዬ፤ ክታብ ዋጋ ያለው ነገር አይምሰልሽ። ሥራ ሥር ወይም የእንስሳት አካል ቁራጭ ወይም ምናምን የተጻፈበት ወረቀት ነው የሞላበት። የሥራ ፈቶች ሥራ ነው። ይልቁንም ሴት ልጅን መጠነኛ ጌጥ ስለሚያሳምራት፤ እኔም አንገቴ ባዶ ባይሆን እመርጣለሁ። ስለዚህ ክታቡን ከመኻከሉ አውጥተሽ ዶቃውን ብቻ እሰሪልኝ" በማለት እናቷን ሳታስቆጣ፤ እንደ ምኞቷ እንዲፈፀምላት ሐሊማ ልታስረዳት ሞከረች።

እናቷም ቆጣ ብላ፤ "የማነው ሰይጣን እንደዚህ የአምልኮቱን ክብር እንድትዳፈሪ የሚመክርሽ? መካሪሽ ክፉ ነገር ሲጠናወትሽ የሚያድንሽ መሰለሽ! ከጥሩ የፍየል ቆዳ ስሰፋ የከረምኳቸውንክታቦች አላስርም ማለቱ የሚገባ ነው?" ብላ አመረረች።

"ስብሰባችን እንዳትቀሪ ዘወትር እጎተጉትሽ የነበረው፤ እኔ የተገነዘብኳቸውን መልካም የአኗኗር ዘዴዎች አንቺም  እንድትረጂ፤ ኋላ ቀር የሆነው አሳብሽም እንዲታረም እያልኩ ነበር። ‹አንዴ ቁርጥማቴ ተነስቶብኛል፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ላሜ ላይ የወጣውን ቁስል የማክምበት ሥራ ሥር ለመማስ ዱር እሄዳለሁ› በማለት ሃምሳ ምክንያት ስታቀርቢ፤ ዘወትር ከስብሰባችን እንዳትቀሪ እለምንሽ የነበረው ለዚህ ነበር፤ ደንቁረን እንዳንቀር። ስንሰበሰብ ብዙ ነገር ያስተምሩናል። ሴቶችም ከወንዶች ጋር አብረን በሁሉም ሥራ እየተካፈልን የበኩላችንን አስተዋጽኦ እናደርጋለን። ስለዚህ የምናበረክተውን አስተዋጽኦ በማድ ቤት ወሽቀን እንዳንቀር ብዙ ያስተምረናል። ማህበራችን ለጋራ ችግራችን መፍትሄ የምንሻበት ነው። በስብሰባችን ላይ ብዙ ነገሮች ተምረናል። የሰው ልጅ የሚደርስበት አደጋም ሆነ በሽታ መነሻው በዐይን የማይታዩ ጥቃቅን ነገሮች ናቸው ያሉንን አልረሳውም። ስለዚህ ክታብ እንደ ክትባት በሽታዎች የሚከላከል አይምሰልሽ። ስንት ጊዜ በቀበሌያችን ስረዳው ቆይቼ ዛሬ ደግሞ ምንም እንዳልሰማ፤ ምንም እንዳልተረዳ ክታብ አስሬ ስሄድ ምን እባላለሁ›› በማለት ሐሊማ እናቷን ልታስረዳት ሞከረች።

‹‹እሺ እንግዲያው አራቱንም ክታቦች፤ ሁለቱ ክንዶችሽ ላይ ከሚታሰሩት ዶቃዎች ጋር አግብቼ ልደርድራቸውና ልሰርልሽ›› አለቻት የሐሊማ እናት። ሐሊማ፤ የእናቷን አመለካከት ስትረዳው፤ እራስዋ በመጀመሪያ ቀን የሴቶች ስብሰባ ላይ እንድትሳተፍ በተጋበዘችበት ዕለት ያደረገችው ትዝ አላት። በወላጆችዋ ጎጆ ውስጥ በመደቧ ላይ ተጋድማ በማቃሰት ታማለች ብለው እንዲተዋት የፈጠረችውን ተንኮል ለአፍታ አሰበች። አባቷ ሐጂ ሙክታር ከሊቅነታቸው ልጃቸውም እንዲደርሳት በማሰብ በሰፈራቸው ከሚገኘው የቁርዓን ትምህርት ቤት ቁርዓን እንድትደግም አድርገዋት ስለ ነበር፤ ኋላም በሹፌርነት አዲስ አበባ የሚሠራው ወንድሟ መንግስት ትምህርት ቤት እንድትገባ ወላጆቿን ስላግባባቸው፤ እስከ ስድስተኛ ክፍል በመማሯ፤

ለአዲስ አመለካከት ከአካባቢዋ ቀድማ በር ከፋች ሆናለች፡፡ በአካባቢው የሴቶች ማህበር ሲቋቋም የብዙዎቹን ሴቶች ድጋፍ በማግኘቷ ለመመረጥ ቻለች፡፡ የሴቶች ማህበር ጸሐፊ ከሆነች ወዲህ፤ ለማህበራቸው የሚላኩ ጽሑፎችን ቀድማ በማንበብ የዕውቀት አድማሷንና አስተሳሰቧን ለማስፋት ሰፋ ያለ ዕድል ገጠማት፡፡ አጠቃላይ ግንዛቤዋ ሲዳብርም፤ ለየጉዳዩ የምትሰጠው ግምት በተጨባጭ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሆነ፡፡ ለባህሏ የጸና ክብር ባትነፍግም፤ ሊሻሻል ይገባዋል ብላ የምታምንበትን ጉዳይ ለሰዎች ለማስረዳት ወደ ኋላ አትልም፡፡

‹‹ሆዬ፤ ለምን አትሰሚኝም፡፡ ዛሬ በሠርጌ ዕለት ለምን በጭቅጭቅ ታደርቂኛለሽ፡፡ ይልቁንስ በገመድሽው አዲስ ክርትላልቆቹን ቢጫማ ዶቃዎች ላንገቴ፤ ትናንሾቹን ቀያዮቹን ደግሞ ክንዴ ላይ አስረሽ አሳምሪኝና ቀሚሴን ልልበስ››በማለት ሐሊማ እናቷን በቁርጥ ጠየቀቻት፡፡

የሐሊማ እናት ልጇን የሱማሌ ወራሪ ወታደሮች ከአሁን አሁን ቀምተው የወስዱብኛል እያለች ከጉያዋ ሥር ደብቃት በሥጋት ትኖር ነበር፡፡ ወራሪው ጦር ከተባረረ ወዲህም የጋብቻን ወግ ለማየትና የመጀመሪያይቱ ሙሽራ ለመሆን በቅታለች፡፡ ሐሊማ አሥራ ዘጠኝ ዓመት ሙሉ ከጉያዋ ያልተለየቻትን እናቷን ዛሬ ልትለያት በመሆኑ፤ ልቧን ባር ባር ብሎታል፡፡ ሰሞኑን ከወላጆችዋ ጋር ሙግት ገጥማለች፡፡ ከአባቷ ከሐጂ ሙክታር ጋርም ተቀያይመው ነው የከረሙት፡፡

ምንጭ፡- ወጋየሁ ተበጀ (1980) አጫጭር ልቦለድ ታሪክ

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. በምንባቡ ውስጥ የተቀመጡትን ገፀ-ባህሪያትን በመዘርዘር ፃፉ፡፡

2. ስለሆዬ ማንነት የተሰማችሁን ፃፉ፡፡

3. እናቷ ቆጣብላና አምርራ የተናገረችውንም ጉዳይ ግለፁ፡፡

4. በምንባቡ ውስጥ እስከመጨረሻ የዘለቀውን ገፀ-ባህሪ ግለፁ፡፡

5. ሐሊማ በሰርጓ ዕለት እናቷ ምን እንድታደርግላት ጠየቀቻት አብራሩ፡፡

ክፍለ ትምህርት ሦስት፡- ዘይቤያዊ አገላለፅ

በዚህ ክፍለ ትምህርት፡-

- የዘይቤ ምንነት

-ዘይቤ በቋንቋ ውስጥ ያለውን አገልግሎት ይገለፅበታል፡፡

ለትምህርት የተመደበ ጊዜ 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፡- ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የዘይቤ ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- የዘይቤ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ዘይቤ በቋንቋ ውስጥ ያለውን አገልግሎት ይገልፃሉ፡፡
- በምንባቡ ውስጥ የዘይቤ አይነቶችን ለይተው ይፅፋሉ፡፡
- በፅሁፋቸው ውስጥ ዘይቤን ይጠቀማሉ፡፡

ምንባብ

## ቀን

አንድ ቀን ብሥራት ታሟል ብለውኝ ልጠይቀው ቤቱ ሔድኩ፡፡ ብሥራት አናቱ በፋሻ ተጠምጥሞ ካልጋው ላይ ተኝቷል፡፡ ከትናንሽ የወረቀት ከረጢቶች ውስጥ የሚዋጡ እንክብሎችን ከየዐይነቱ አውጥቶ ሊቅም ውሃ እስኪመጣለት እየጠበቀ ነው፡፡

‹ምን አገኘህ ወንድሜ?› ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ‹እባክህ ቀን ነው እንጂ ሌላ ምን ይባላል!› አለኝ፡፡ ይኸን እንዳለ፤ ውሃ በብርጭቆ ይዛ የመጣችው የብሥራት ሠራተኛ ዘነበች ጣልቃ ገባችና ተከታዩን ታሪክ ማውራት ጀመረች፡፡ ብስራትን ለመጠየቅ ዐልፎ ዐልፎ ቤቱ ስሔድ ዘነበችን ስለማገኛት አውቃታለሁ፡፡ በተለይም ወሬ አቀራረቧ አይረሳኝም፡፡ የዚያን ዕለትም ወሬ ለማውራት ቸኩላ፤ ሰላምታም ሳንለዋወጥ ነው ወሬዋን የቀጠለችው፡፡

‹ትላንት ጋሼ በስድስት ሰዓት ላይ ምሳቸውን ምንም ያህል አልበሉም፡፡ ትንሽ ብቻ ቀመሱና መዋኛ ስፍራ እውላለሁ ብለው ወጡ፡፡ ለካስ እዚያ ሲደርሱ የመዋኛ ሱሪያቸውን ረስተውት ኖሮ ብስጭት ብለው ተመልሰው ለመውሰድ ወደ ቤት መጡ፡፡ ጋሼ ሲመለሱ ግን እኔ ቤት

የለሁም፤ ገበያ ሔጃለሁ። ገበያ መሄዱን ሲሰሙ ጋሼ ቁልፍ ፍለጋ ወደ እኔጋ ገበያ መምጣት። እሳቸው ገበያ ሲመጡ፤ እኔ ሸመታዬን አጠናቅቄ ወደ ቤቴ መመለስ። እሳቸው ገበያ እንደ ደረሱ ደምበኛችን ቤት ሔደው፤ ‹አልመጣችም ወይ› ብለው ሲጠይቁት ‹ወደ ቤቷ ተመልሳ ሔዳለች› ብሎ መመለስ። እንዲያው በሞትኩት፤ ያንዳንድ ቀን አጋጣሚ፤ እኔ ቤት ስደርስ የሰፈር ሰዎች ጋሼ እኔን ፍለጋ ወደ ገበያ መሔዳቸውን ይነግሩኛል። ‹ውይ በሞትኩት› ብዬ እኔን ፍለጋ እንዳይንከራተቱ ቶሎ ወደ ገበያ ተመልሼ መሔድ፤ እኔ ገበያ እንደ ሔድሁ እሳቸው ወደ ቤት ምጥት። ቤት ስደርስ ጣቶቻቸውን ግንባራቸው ላይ አጋድመው ቤታችን በራፍ ላይ ቁጭ ብለው አገኘኋቸው።

‹‹ውይ በሞትኩት›› አልኩና በሩን ቶሎ ልከፍትላቸው ዘምቢሌ ውስጥ ያስቀመጥኩትን ቁልፍ ስፈልግ ከየት ይገኝ! ‹‹ምን ሰይጣን ወስዶት ይሆን?›› ብዬ በድንጋጤ ቁልፍ የሌለበትን ዘምቢል እየዳበስኩ፤ ‹‹ውይ በሞትኩት፤ ለገዛሁት ዕቃ ሒሳብ ለመክፈል ቦርሳዬን ስከፍት፤ ቁልፉን ደምበኛችን ሱቅ ማውጣቴ ትዝ ይለኛል። እሱ ቤት ጥየው መጥቻለሁ። ቶሎ ሔጄ ላምጣ›› አልኳቸውና ዐይናቸውንም ለማየት ፈርቼ ቶሎ ብዬ ሮጥኩ። ቶሎ አውቶቡስ ተሳፍሬ ሔድኩና ከደምበኛችን ቤት ስደርስ፤ ‹‹ለምሳው እንደ ዘጋ አልተመለሰም›› አሉኝ። ‹‹ውይ በሞትኩት ዛሬ›› ብዬ ስጠብቅ፤ ስጠብቅ፤ በጊዜ ይመጣ መሰላችሁ? ምን ያለ የተረገመ ቀን ነው ዛሬ እያልኩ ስራገም ደምበኛችን በዘጠኝ ሰዓት ከሱቅ መድረስ። ቁልፉን መደርደሪያው ላይ ካስቀመጠበት አንስቶ ሲሰጠኝ ብር ብዬ ወደ ቤት መጥቼ በሩን ከፈትኩና፤ ‹‹ውይ በሞትኩት ጋሼ! ይቅርታ›› አልኳቸው።

‹‹አንቺ አይደለሽም ዘነበች፤ ቀኑ ነው›› አሉኝ። ቶሎ ብዬ የመዋኛ ሱሪያቸውን ስሰጣቸው፤ ‹‹አይ ከዚህ በኋላስ አልሔድም እተኛለሁ›› አሉኝ። ‹‹ውይ በሞትኩት›› ብዬ ወደ ማድ ቤት ገባሁ። ጋሼም ጋደም ብለው ማንኮራፋት ጀመሩ።

*ምንጭ፡- ወጋየሁ ተበጀ (1980) አጫጭር ልቦለድ ታሪክ*

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በጽሁፍ መልስ ስጡ።**

1. ከላይ በምንባቡ ውስጥ በዘይቤ የተገለፁ አረፍተ ነገሮችን ፃፉ።

2. በምንባቡ ውስጥ የተገለፁ የዘይቤአይነቶችን በዝርዝር ፃፉ።

3. ዘይቤያዊ አገላለፆችን መጠቀም ያለውን ፋይዳ ፃፉ፡፡

4. የተለያዩ የዘይቤ አገላለፆች ያሉበት አጭር አንቀፅ /ከአምስት አረፍተ ነገሮች የተመሰረተ/አንቀፅ ፃፉ፡፡

ክፍለ ትምህርት አራት፡- አንቀፅ

በዚህ ክፍለ ትምህርት፡-

- የአንቀጽ ምንነት እና

- የአንቀጽ አደረጃጀት ይቀርብበታል፡፡

ለትምህርት የተመደበ ጊዜ 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፡- ይህንን ትምህርት ከተማሩ በኋላ ተማሪዎች፡-

- የአንቀጽን ምንነትናአንቀጽ ከምን እንደሚዋቀር ይገለፅበታል፡፡
- የተለያዩ ርዕሶችን በመምረጥ አንቀጽ ይገነባሉ፡፡

ምንባብ

**ትንሹ ሰውዬ**

‹‹አየህ … የተቆጣጣሪና የወሰን አስከባሪ ሥራ ፍርሃትና ማመንታትን አይወድም፡፡ ቆራጥነትን ይሻል፡፡ ልጄ ሙት! ሙት አልልህም ድፍን ገንዘብ ተቀባይ ብትጠይቅ ስለኔ ብዙ ብዙ ትሰማለህ …›› አሉኝና አንዳች ያዎንታ መልስ ከኔ እንደሚጠብቁ ሁሉ አፍ አፌን ጠበቁ፡፡‹‹ስለራሳቸው ጀብድና ታላቅነት ብዙ ማውራት የሚሹ ሳይሆኑ አይቀሩም›› የሚል የሥነ-ልቡና መላምት ጣልኩና አንገቴን በመነቅነቅ ለማንነታቸው ድጋፍ ሰጠኋቸው፡፡ ፋታ ልሰጣቸው አልፈለኩም፡፡ እንደ ጦር የተከሉብኝን ዐይኖቻቸውን ወደ ግድግዳው ሲሰቅሉ፤ ‹‹እኝህ ሰው በሥራ ዓለም በነበሩበት ጊዜ ብዙ ምስቅልቅል ሁኔታዎች ውስጥ ገብተው ሳይወጡ አይቀሩም፡፡ ያለፈ ሕይወታቸውን የሚያሽትላቸው ደግ አፍንጫ ቢያገኙ …›› እያልኩ ሌላ መላ ምት በውስጤ ሳደራ አናገሩኝ፡፡

‹‹ልጄ ልበልህ … መቼም ካብራኬ ባትወለድም አንተን የሚያካክሉ ዝግኖች አድርሻለሁና ልጄ በማለቴ ቅርታ አይግባህ፡፡ ይኸ የተቆጣጣሪነት ሥራ ብዙ ብዙ ታሪክ አሳይቶኛል፡፡

የስም ትልቅ የምግባር ትንሽ፤ የደረጃ ትንሽ የውጤት ትልቅ አስቆጥሮኛል›› አሉና አሁንም የኔን ስሜት ይገምቱ ያህል፤ እነዚያን የመርፌ ቀዳዳ የሚያካክሉ ዐይኖቻቸውን እንደ ስፒል ተከሉብኝ። ያይኖቻቸውን ፈተና ለማለፍ ያህል፤ ‹‹እንዴት? እንዴት ማለት ነው - አልገባኝም›› አልኳቸው።

ምንጭ፡- አበራ ለማ (1981) አጫጭር ልቦለድ ታሪኮችና ሥነ-ግጥሞች

**ተግባር አንድ**

**የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ።**

1. ስለወቅቱ የኑሮ ውድነት አንድ አንቀጽ ፃፉ።

2. ስለምትወዱት የትምህርት አይነት እና አጠናን ዘዴያችሁ ሁለት አንቀጽ ፅፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

አባሪ "ሠ"፡- የቅድመ እና የድህረ ትምህርት የሙከራ ቡድን የፈተና ውጤት

| ኮድ | የቅድመ ትምህርት | የድህረ ትምህርት |
|---|---|---|
| 1 | 30 | 36 |
| 2 | 28 | 26 |
| 3 | 24 | 30 |
| 4 | 22 | 22 |
| 5 | 18 | 26 |
| 6 | 14 | 20 |
| 7 | 24 | 22 |
| 8 | 12 | 24 |
| 9 | 18 | 28 |
| 10 | 24 | 36 |
| 11 | 26 | 32 |
| 12 | 32 | 44 |
| 13 | 38 | 46 |
| 14 | 32 | 38 |
| 15 | 20 | 20 |
| 16 | 18 | 26 |
| 17 | 28 | 32 |
| 18 | 18 | 28 |
| 19 | 18 | 32 |
| 20 | 28 | 36 |
| 21 | 24 | 20 |
| 22 | 14 | 26 |
| 23 | 20 | 46 |
| 24 | 20 | 34 |
| 25 | 30 | 38 |
| 26 | 40 | 46 |
| 27 | 26 | 34 |
| 28 | 12 | 22 |
| 29 | 46 | 48 |
| 30 | 10 | 26 |
| 31 | 14 | 24 |
| 32 | 38 | 38 |

አባሪ "ረ"፡- የቅድመ እና የድህረ ትምህርት የቁጥጥር ቡድን የፈተና ውጤት

| ኮድ | የቅድመ ትምህርት | የድህረ ትምህርት |
|---|---|---|
| 1 | 22 | 26 |
| 2 | 24 | 32 |
| 3 | 10 | 12 |
| 4 | 40 | 38 |
| 5 | 12 | 16 |
| 6 | 38 | 32 |
| 7 | 12 | 16 |
| 8 | 38 | 38 |
| 9 | 30 | 30 |
| 10 | 26 | 22 |
| 11 | 20 | 22 |
| 12 | 26 | 26 |
| 13 | 18 | 32 |
| 14 | 28 | 22 |
| 15 | 36 | 34 |
| 16 | 16 | 20 |
| 17 | 22 | 22 |
| 18 | 18 | 16 |
| 19 | 18 | 20 |
| 20 | 26 | 26 |
| 21 | 20 | 24 |
| 22 | 22 | 22 |
| 23 | 16 | 20 |
| 24 | 32 | 32 |
| 25 | 38 | 40 |
| 26 | 32 | 32 |
| 27 | 26 | 26 |
| 28 | 22 | 26 |
| 29 | 18 | 20 |
| 30 | 12 | 16 |
| 31 | 16 | 18 |
| 32 | 24 | 16 |

አባሪ "ሰ"፡- የቅድመ ትምህርት እና የድህረ ትምህርት የሁለቱ ቡድኖች የፈተና ውጤት

| ኮድ | የቅድመ ትምህርት የፈተና ውጤት | | የድህረ ትምህርት የፈተና ውጤት | |
|---|---|---|---|---|
| | የሙከራ ቡድን | የቁጥጥር ቡድን | የሙከራ ቡድን | የቁጥጥር ቡድን |
| 1 | 30 | 22 | 36 | 26 |
| 2 | 28 | 24 | 26 | 32 |
| 3 | 24 | 10 | 30 | 12 |
| 4 | 22 | 40 | 22 | 38 |
| 5 | 18 | 12 | 26 | 16 |
| 6 | 14 | 38 | 20 | 32 |
| 7 | 24 | 12 | 22 | 16 |
| 8 | 12 | 38 | 24 | 38 |
| 9 | 18 | 30 | 28 | 30 |
| 10 | 24 | 26 | 36 | 22 |
| 11 | 26 | 20 | 32 | 22 |
| 12 | 32 | 26 | 44 | 26 |
| 13 | 38 | 18 | 46 | 32 |
| 14 | 32 | 28 | 38 | 22 |
| 15 | 20 | 36 | 20 | 34 |
| 16 | 18 | 16 | 26 | 20 |
| 17 | 28 | 22 | 32 | 22 |
| 18 | 18 | 18 | 28 | 16 |
| 19 | 18 | 18 | 32 | 20 |
| 20 | 28 | 26 | 36 | 26 |
| 21 | 24 | 20 | 20 | 24 |
| 22 | 14 | 22 | 26 | 22 |
| 23 | 20 | 16 | 46 | 20 |
| 24 | 20 | 32 | 34 | 32 |
| 25 | 30 | 38 | 38 | 40 |
| 26 | 40 | 32 | 46 | 32 |
| 27 | 26 | 26 | 34 | 26 |
| 28 | 12 | 22 | 22 | 26 |
| 29 | 46 | 18 | 48 | 20 |
| 30 | 10 | 12 | 26 | 16 |
| 31 | 14 | 16 | 24 | 18 |
| 32 | 38 | 24 | 38 | 16 |